# የ2013 በጀት ዓመት የ6 ወራት የአፈፃፀም ሪፖርት

ታህሳስ 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## የሰነድ ዝግጅት መረጃ

| | | |
|---|---|---|
| የመጀመሪያ ረቂቅ | በክትትል እና ግምገማ ቡድን | ታህሳስ 2013 ዓ.ም |
| የመጀመሪያ ዙር ክለሳና ግምገማ | በፕላንና ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት | ታህሳስ 2013 ዓ.ም |
| ሁለተኛ ዙር ክለሳና ግምገማ | በዋና ዳ/ጽ/ም/ዋ/ዳይሬክተር | ታህሳስ 2013 ዓ.ም |
| የመጨረሻ ዙር ክለሳ በማድረግ ሪፖርቱን ገምግሞ ያጸደቀው | ኤክሲኪዩቲቭ ማኔጅመንት | ታህሳስ 2013 ዓ.ም |

ያቀረበው

እንዲፀድቅ የደገፈው

___________________________

የፕላንና ፕሮግራም ዳ/ዳይሬክተር

___________________________

የዋና ዳ/ጽ/ቤት ም/ዋ/ዳይሬክተር

ፀድቋል

___________________________

ዋና ዳይሬክተር

# ማውጫ


**የሪፖርቱ ጭማቂ ሃሳብ (EXCUTIVE SUMMARY) .......... 5**

**ምዕራፍ አንድ .......... 7**

**የዝግጅት ምዕራፍ አፈፃፀም .......... 7**

1.1 የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት .......... 7

1.2 የ2013 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች .......... 8

1.3 የ2013 በጀት ዓመት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች .......... 8

*1.3.1 ግብአት ማሟላት .......... 8*

*1.3.2 ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማካሄድ .......... 11*

**ምዕራፍ ሁለት .......... 13**

**የተቋማዊና ስትራቴጂያዊ (ቁልፍ) ጉዳዮች አፈፃፀም .......... 13**

2.1 ከለውጥ ሥራ አመራር እና ተቋማዊ ልማት ጋር ተያይዞ የተከናወኑ ተግባራት አፈፃፀም .......... 13

2.2 ፖሊሲና ስትራቴጂ .......... 13

2.3 የሰው ኃይል እና አመራር .......... 14

2.4 ከባቢያዊ ሁኔታና ተቋም ግንባታ .......... 14

2.5 አደረጃጀት እና መዋቅር .......... 15

2.6 ዋና የስራ ሂደቶች .......... 15

2.7 የኢመባ ዲጂታይዜሽን እና ቴክኖሎጂ .......... 17

**ምዕራፍ ሶስት .......... 18**

**የመደበኛ ሥራዎች አፈፃፀም .......... 18**

3.1 የቅድመ ግንባታ ሥራዎች አፈጻጸም .......... 18

***3.1.1 የምህንድስና ግዥ አፈፃፀም .......... 18***

*3.1.2 የዲዛይን ሥራዎች አፈጻጸም .......... 20*

*3.1.3 የዲዛይን ሥራዎች አፈጻጸም .......... 20*

*3.1.4 የቅድመ ግንባታ የወሰን ማስከበር ሥራዎች አፈጻጸም .......... 20*

3.2 የግንባታ ሥራዎች አፈፃፀም .......... 23

*3.2.1 የፕሮጀክቶች የፊዚካል አፈጻጸም .......... 23*

*3.2.2 የፕሮጀክቶች አፈፃፀም - በሃገር ውስጥ እና በውጭ ሃገር ተቋራጭ .......... 24*

*3.2.3 የፕሮጀክቶች አፈጻጸም - በአስፈጻሚ ዳይሬክቶሬት .......... 27*

*3.2.4 የፕሮጀክቶች አፈፃፀም - በፋይናንስ ምንጭ .......... 27*

*3.2.5 አፈፃፀሙ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር .......... 28*

*3.2.6 በበጀት ዓመቱ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ ተግዳሮት ያሰደሩ .......... 29*

3.3 የመንገድ ሀብት ማኔጅመንት አፈፃፀም .......... 31

*3.3.1 የድንገተኛ ሥራዎች አፈጻጸም .......... 31*

*3.3.2 የመንገድ ጥገና ሥራዎች አፈጻጸም .......... 33*

*3.3.3 የመንገድ ጥገና ስራዎች በተቋራጭ .......... 35*

*3.3.4 የተሽከርካሪዎች ክብደት እና መጠን ቁጥጥር ሥራ እና የትራፊክ ቆጠራ አፈፃፀም .......... 35*

*3.3.5 የመንገድ ደህንነት ሥራዎች አፈጻጸም ..... 36*

**ምዕራፍ አራት ..... 38**

**የዘርፈ ብዙ ሥራዎች አፈፃፀም ..... 38**

4.1 የሴቶች እና ወጣቶች ጉዳይ አፈጻጸም ..... 38
4.2 የህግ ጉዳዮች አፈፃፀም ..... 43
4.3 የአካባቢ፣ ማሕበራዊ እና የሥራ ቦታ ደህንነት ጋር በተያያዘ የተከናወኑ ተግባራት ..... 45
*4.3.1 የአካባቢ ማኔጅመንት ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት ..... 45*
*4.3.2 ከሰሻል እና መልሶ ማቋቋም ማኔጅሜንት ጋር በተያያዘ የተከናወኑ ተግባራት ..... 46*
*4.3.3 ከሥራ ቦታ ጤናና ደህንነት ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት አፈፃፀም ..... 46*
4.4 የስታንዳርዳይዜሽን እና የጥራት ቁጥጥር ሥራዎች ..... 47
4.5 ከመንገድ የምርምር ጋር የተያያዙ ሥራዎች አፈፃፀም ..... 48
4.6 ከኮሙኒኬሽ ጋር የተያያዙ ሥራዎች ..... 50
4.7 ከሥነ-ምግባር እና ከደንበኞች አገልግሎት አኳያ ..... 52
4.8 ከግዥ እና አቅርቦት ጋር በተገናኘ የተከናወኑ ሥራዎች ..... 52
4.9 በማሰልጠኛ ማዕከላት የተሰጡ ሥልጠናዎች ..... 53
*4.9.1 አለምገና ማሰልጠኛ ማዕከል ..... 53*
*4.9.2 በጊንጪ ማሰልጠኛ ማዕከል ..... 53*
4.10 የኢመባን የሲስተም እና ሁለንተናዊ የአይቲ አቅም ማሳደግ ..... 54
4.11 የኦዲት ሥራዎች ..... 56
*4.11.1 የፋይናንሻል ኦዲት ..... 56*
4.12 የ2013 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም ..... 57
4.13 ተሞክሮዎች ..... 59
4.14 የኮቪድ 19 ተፅዕኖ እና የተወሰዱ የመከላከያ እርምጃዎች የCOVID-19 ተፅዕኖ ..... 59

**የማጠቃለያ ምዕራፍ ..... 61**

5.1 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ..... 61
*5.1.1 ያጋጠሙ ችግሮች ..... 61*
*5.1.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች ..... 62*
5.2 በትግበራ ወቅት የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ..... 62
*5.2.1 ጠንካራና ጎኖች ..... 62*
*5.2.2 ደካማ ጎኖች ..... 63*
*5.2.3 ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ..... 63*
5.3 ክትትል፣ ድጋፍ እና ግምገማ ..... 64
*5.3.1 የውስጥ የክትትልና ግምገማን በተመለከተ ..... 64*
*5.3.2 በውጭ ባለድርሻ አካላት የሚደረጉ ክትትልና ግምገማን በተመለከተ ..... 65*
5.4 በ2013 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ሪፖርት ላይ በግብረመልስ ለተነሱ ጥያቄዎች ከተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ አንፃር የተሰጠ ምላሽ ..... 66
5.5 ማጠቃለያ ..... 67

**አባሪዎች፡-**


**አባሪ 1፡ በ2013 በጀት ዓመት 6 ወራት የተፈጠረ የስራ ዕድል**

**አባሪ 2፡ የ2013 በጀት ዓመት የ2ኛ ሩብ ዓመት እና የ6 ወራት የፊዚካል ሥራዎች አፈፃፀም**

**አባሪ 3፡ የ2013 በጀት ዓመት የአምስት ወራት የገንዘብ አጠቃቀም**

**አባሪ 4 ፡ የ2013 በጀት ዓመት የ6 ወራት የዲዛይን ስራዎች አፈፃፀም**

## የሪፖርቱ ጭማቂ ሃሳብ (Excutive Summary)

በ2013 በጀት ዓመት ከሌላው ዓመታት በተለየ ከፍተኛ መጠን ያለው በጀት በመንግስት የተመደበ ሲሆን ይህም ለዘርፉ የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ያመለክታል። በዚህም መሠረት ከመንግስት ለካፒታል ፕሮጀክቶች ወደ 50 ቢሊዮን፣ ለመደበኛ በጀት 738 ሚሊዮን ብር፣ ከብድር 7.82 ቢሊዮን፣ ከእርዳታ 258.5 ሚሊዮን እንዲሁም ከመንገድ ፈንድ 2.4 ቢሊዮን በአጠቃላይ 61.23 ቢሊዮን ብር ተመድቧል።

በበጀት ዓመቱ 117 የመንገድ የአዲስ መንገድ ግንባታ እና የደረጃ ማሻሻል ፕሮጀክቶችን ግዥ ለመፈፀም ዲዛይን ለሌላቸው የመነሻ/ዝርዝር ዲዛይን የማስጠናት፣ ጨረታቸውን የማውጣት እንዲሁም ለተፈረሙ ፕሮጀክቶች የቅድመ ዝግጅት ሥራ ለማከናወን በዕቅድ ተይዟል። ከዚህም ባለፈ በ2013 በጀት ዓመት 2,563 ኪ.ሜ የሚሸፍኑ የተለያዩ የመንገድ ግንባታዎችን ለማካሄድ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን በነባር መንገዶች ማጠናከር 38.1 ኪሜ፣ በነባር መንገዶች ደረጃ ማሻሻል 454.6 ኪ. ሜ፣ በአዳዲስ መንገዶች ግንባታ 1225.9 ኪ. ሜ እና 844 ኪ.ሜ የከባድ ጥገና ስራ ለማከናወን ታስቧል።ከዚህ በተጨማሪ 14,818 ኪ.ሜ በወቅታዊ እና መደበኛ የመንገድ ጥገና ለማከናወን ታቅዷል።

ለበጀት ዓመቱ የተያዘውን ዕቅድ በተሳካ መልኩ ለማስፈጸም በርካታ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ተቋሙን በሰው ኃይል እና በግብዓት ለማጠናከር የተደረገው ጥረት ማሳያ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ዓመቱ የቀጣይ 10 ዓመት ዕቅድ ተግባራዊ መደረግ የሚጀምርበት እንደመሆኑ ከውስጥ እና ከውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት መፍጠር የሚያስችሉ የተለያዩ ውይይቶች ተካሂዷል።

### የፕሮጀክቶች የ2013 በጀት ዓመት የ6 ወራትየፊዚካል ሥራዎች አፈፃፀም

በ2013 በጀት ዓመት የ6 ወራት የፊዚካል ስራዎች ዕቅድ አፈፃፀም በነባር መንገዶች ማጠናከር 12 ኪሜ ዕቅድ ተይዞ 14 ኪ. ሜ ፤ በነባር መንገዶች ደረጃ ማሻሻል 169 ኪ.ሜ ታቅዶ 139 ኪ.ሜ እንዲሁም በአዳዲስ መንገዶች ግንባታ 437 ኪ.ሜ ታቅዶ 332 ኪ.ሜ አፈፃፀም ተመዝግቧል: ፡ በመንገዶች ከባድ ጥገና 307 ኪ.ሜ ታቅዶ 157 ኪ.ሜ ፤ በመንገዶች ወቅታዊ ጥገና 560 ኪ.ሜ ታቅዶ 260 ኪ.ሜ፣ እንዲሁም በመንገዶች መደበኛ ጥገና 4,734 ኪ.ሜ ታቅዶ 3,919 ኪ. ሜ ተከናውኗል። በአጠቃላይ የ6 ወራት የፊዚካል ሥራዎች አፈፃፀም 78 በመቶ ሆኗል። ሲሆን በቀጣይም ርብርብ በማድረግ አብዛኛውን ሥራ በዕቅዱ መሠረት ለመፈጸም ጥረት ይደረጋል።

ሠንጠረዥ1:-የ2013 በጀት ዓመት የ6 ወራት የፊዚካል ሥራዎች አፈፃፀም ማጠቃለያ

| ተ.ቁ | ንዑስ ተግባር | መለኪያ | የ2013 በጀት ዓመት እቅድ | የ6 ወራት | | | የዓመቱ ቀሪ ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | % | |
| **1** | **የመንገዶች ግንባታ፣ ማጠናከርና ማሻሻል** | | | | | | |
| 1.1 | ነባር መንገዶች ማጠናከር | ኪ. ሜ | 38 | 12 | 14 | 113 | 24 |
| 1.2 | የነባር መንገዶች ደረጃ ማሻሻል | " | 455 | 169 | 139 | 82 | 316 |
| 1.3 | አዲስ መንገዶች ግንባታና የፍጥነት መንገድ | " | 1226 | 437 | 332 | 76 | 894 |
| | **የግንባታ ሥራዎች ንዑስ ድምር** | | **1719** | **619** | **485** | **78** | **1234** |
| **2** | **የመንገድ ጥገና ሥራዎች** | | | | | | |
| 2.1 | የመንገደች ከባድ ጥገና | " | 844 | 307 | 157 | 51 | 687 |
| 2.2 | ወቅታዊ የመንገዶች ጥገና | ኪ. ሜ | 1515 | 560 | 260 | 46 | 1255 |
| 2.3 | መደበኛ ጥገና | " | 13303 | 4734 | 3919 | 83 | 9384 |
| | **የጥገና ሥራዎች ንዑስ ድምር** | | **15662** | **5600** | **4335** | **77** | **11326** |
| | **አጠቃላይ የፊዚካል ሥራዎች ድምር** | | **17380** | **6219** | **4820** | **78** | **12560** |

1

# ምዕራፍ አንድ

# የዝግጅት ምዕራፍ አፈፃፀም

## 1.1 የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት

መንግስት ለመንገድ ዘርፍ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት እና በየደረጃው በተደረገው ርብርብ እስካሁን ተግባራዊ በተደረጉ አምስት የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮግራሞች ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ተችሏል። በሃገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተፈጠረውን ለውጥ ተከትሎ በተቋም ደረጃ ያለፉትን የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮግራሞችን አፈፃፀም በጥልቀት ፈትሾ መስተካከል እና መጠናከር ያለባቸውን በርካታ ጉዳዮች በመለየት ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። በተለይም ከተቋማዊ የማሻሻያ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ትርጉም ያለው ለውጥ የተመዘገበ ሲሆን ይህም ተቋማዊ የማስፈፀም አቅምን በማሳደግ ባለስልጣን መ/ቤቱ በቀጣይ ለሚያከናውናቸው የመንገድ ልማት ፕሮግራሞች የተሻለ አፈፃፀም ለማስመዝገብ ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው ይጠበቃል።

በዚሁ መሰረት የተቋሙ የቀጣይ አስር ዓመታት መሪ ዕቅድ ሃገራዊ አቅጣጫን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን፤ የዘርፉን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም በቀጣይ ሊደረስበት የታሰበውን ግብ መነሻ አድርጓል። በተለይም "ኢትዮጵያ-አፍሪካዊት የብልፅግና ተምሳሌት" የመሆንን ሃገራዊ ራዕይ እና ይህንን ለማሳካት የተቀረፀውን ሃገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ከተቀመጡ የትኩረት አቅጣጫዎች እና ፕሮጀክቶች ጋር በማስተሳሰር የመንገድ ዘርፍ ዕቅድ እንዲቀረፅ ተደርጓል።

የቀጣይ አስር ዓመቱ ዕቅድ በሁለት የአምስት ዓመታት የትግበራ ምዕራፎች ተከፍሎ የሚተገበር ሲሆን መንግስት ከዚህ ውስጥ የመጀመሪያውን አምስት ዓመት ዕቅድ ለማስፈፀም የሚያስችል የትግበራ ስርዓት የዘረጋ ሲሆን በተለይም የ2013 በጀት ዓመት በ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ተይዘው እና ህብረተሰቡ የሚያውቃቸው ሆነው በበጀት እጥረት ምክንያት ሳይከተቱ የቀሩ ፕሮጀክቶች የተካተቱበት ሲሆን ከዚህ ባሻገር የፕሮግራም በጀቱ የቀጣይ ዓመታት አቅጣጫ የተመላከተበት እና መሰረት የተጣለበት ነው።

በአጠቃላይ የ2013 በጀት ዓመት እቅድ ሲዘጋጅ የመንገድ ዘርፉን እና የኢመባን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ የ2012 በጀት ዓመት አፈፃፀምን በመገምገም እና ሊወሰዱ የሚችሉ መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሁም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን መከላከል በሚያስችል መልክ ነው።

## 1.2 የ2013 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች

ከ2012 በጀት ዓመት አፈፃፀም ተሞክሮ በመነሳት አጠቃላይ በዘርፉ በ2013 በጀት ዓመት የተቀመጡ የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ✓ ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ ከመግባታቸው በፊት የመንገድ ወሰን ማስከበር ሥራዎችን የበጀት ዓመቱን የግንባታ ሥራ ሊያስቀጥል በሚችል መልኩ ማጠናቀቅ፣ በአጠቃላይ የመንገድ መሠረተ ልማት ቅድመ ግንባታ ሥራዎችን ግልጽነትንና ጥራት ማሻሻል እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ፣
- ✓ ውል የተገባላቸው ፕሮጀክቶች በወቅቱ የሞቢላይዜሽን ሥራቸውን እንዲያጠናቀቁና ሥራ እንዲጀምሩ ማድረግ፣
- ✓ በመንገድ ግንባታ ሂደት የሚፈጠሩ የጊዜ ማራዘሚያ እና ተያያዥ ወጪዎችን መቀነስ፣
- ✓ ግንባታቸው የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን በወቅቱ መዝጋት፣
- ✓ ፍትሃዊ የመንገዶች ሥርጭት እና ተደራሽነት እንዲኖር ማስቻል፣
- ✓ ለመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ትኩረት በመስጠት የጥገና አቅምን ማሳደግ፣
- ✓ የኮሪዶር ትራንስፖርት ልማትና አለምአቀፋዊ ትስስርን ማጠናከር፣
- ✓ በአገሪቱ እየተከሰተ ያለውን የትራፊክ አደጋ መቀነስ የሚያስችል ሥራ ማከናወንእና
- ✓ ተቋማዊ የመፈፀም አቅምን መገንባት ናቸው፡፡

## 1.3 የ2013 በጀት ዓመት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች

### 1.3.1 ግብአት ማሟላት

#### 1.3.1.1 የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ማስመደብ

መ/ቤቱ የሚያስተዳድራቸው ፕሮጀክቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ በመምጣቱ የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት ፍላጎቱ በዛው ልክ ከፍ እያለ መጥቷል፡፡ በመሆኑም በየደረጃው ተከታታይ ውይይቶችን በማካሄድ በዚህ በጀት ዓመት ከመንግስት 50.7 ቢሊዮን ብር እንዲመደብ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ይህም በሂደት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠል እና አዲስ ለሚጀመሩ ፕሮጀክቶች ቅድመ ክፍያ የሚውል ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከልማት አጋሮች እና ከመንገድ ፈንድ አስፈላጊው በጀት እንዲመደብ ተገቢው ክትትል ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ ለበጀት ዓመቱ የተመደበውን የገንዘብ መጠን በየፋይናንስ ምንጩ የሚያሳይ መረጃ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 2 ለበጀት ዓመቱ የተመደበ የካፒታል እና የመደበኛ በጀት

| የበጀት ዓይነት | በፋይናንስ ምንጭ (በሚሊ. ብር) | | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | መንግስት | መንገድ ፈንድ | ብድር | ዕርዳታ | |
| ካፒታል | 50,000 | 2,408.24 | 7,821.73 | 258.47 | 60490.18 |
| መደበኛ | 737.81 | - | - | - | 737.81 |
| **ድምር** | **50,737.81** | **2,408.24** | **7,821.73** | **258.47** | **61,227.98** |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መመልከት እንደሚቻለው የባለስልጣኑ የ2013 አጠቃላይ በጀት 61.23 ቢሊዮን ብር ሲሆን ይህም በባለስልጣኑ ታሪክ ከፍተኛው ነው፡፡ በዚህም መሠረት የጸደቀውን የካፒታል እና መደበኛ በጀት በየፕሮጀክቱ እና በየሥራ ክፍሉ በመደልደል እንዲሁም ሁሉም የሥራ ክፍሎች ይህንኑ እንዲያውቁት በማድረግ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

### 1.3.1.2 የሰው ኃይል ማሟላት እና ማሰልጠን

የባስልጣን መ/ቤቱን ተቋማዊ ብቃት ለማሳደግ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ሲሰሩ መቆየታቸው የሚታወቅ ሲሆን በዚህ ረገድ የሰው ኃይሉን ለማሟላት እና ለማብቃት የተሠራው ሥራ ተጠቃሽ ነው፡፡ በ2013 በጀት ዓመትም በተጓደሉ እና አስፈላጊ በሆኑ የሥራ መደቦች ላይ የሠው ኃይል በቅጥር፣ በዝውውር እንዲሁም በእድገት እየተሞላ የሚገኝ ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎን የኮረና ወረርሽኝ እንዳይስፋፋ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ የተለያዩ ስልጠናዎች እየተሰጡ ነው:: አጠቃላይ አፈጻጸሙ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡- የሰው ኃይል ማሟላት**

| ተ.ቁ | ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የ6 ወራት | | ክንውን በትንታኔ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | ክንውን | | |
| 1 | **የሰው ኃይል አቅርቦትን መፈጸም፤** | 150 | 138 | | 25 ሠራተኞች ከኢኮስኮ ወደ ኢመባ የተዛወሩ ናቸው፡፡ |
| | 1.1 በዝውውር የሠራተኛ ምደባ ማካሄድ፤ | | | | |
| | 1.2 በውስጥ ዕድገት፣ ቅጥር እና የኮንትራት ሰራተኛን ቋሚ ማድረግ የሠራተኛ ምደባ ማካሄድ<br>➢ የውስጥ እድገት እና የውጭ ቅጥር<br>➢ የኮንትራት ሰራተኛን ቋሚ ማድረግ | 326<br>200 | 211<br>- | በተቋቋመው ኮሚቴ መሰረት የምደባ ስራው በመካሄድ ላይ ነው | በቀጣዩ 2ወራት ሥራው ተጠናቆ አግባብ ላላቸው የኮንትራት ሠራተኞች የቋሚነት ምደባ ይደረጋል፡፡ |
| 2 | **የሰው ሀብት ሥልጠናና ልማት ማስፈጸም** | | | | |
| | 2.1. በሀገር ውስጥ አጫጭር ሥልጠናዎችን መስጠት<br>2.2. በውጭ ሀገር አጫጭር ሥልጠናዎችን መስጠት<br>2.3. ለአዲስ ተቀጣሪ ሠራተኞች የትውውቅ ሥልጠና መስጠት<br>2.4. የማስተርና ፒ. ኤችዲ ትምህርት ማስጀመር | 4729<br>65<br>160<br>13 | -<br>-<br>127<br>8 | በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት በዕቅዱ መሠረት ሥልጠናን ማከናወን አልተቻለም | በቁጥር ለ127 ባለሙያዎች በስነምግባርና ሙስና ፅንሰ ሀሳብ ዙሪያ ሥልጠና ተሠጥቷል፤<br>ለ150 የሥራ ኃላፊዎች በ paradigm shift coaching incentive ሥልጠና ተሠጥቷል፤<br>በዕቅዱ መሠረት ለሚሠጡ ሥልጠናዎች የአሠልጣኞች መረጣ ሥራ ተካሂዷል፤ |
| | 2.5. ለሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች የ75% የትምህርት ወጪ ሽፋን በመስጠት ክፍያ መፈፀም (በብር) | 1,000,000.00 | 586,000.00 | 59 % | የአገልግሎት አሠጣጥ ስታንዳርዱን በ88% በጠበቀ ሁኔታ ተከናውኗል |
| 3 | **የሠራተኞች ግንኙነትና ዶክመንቴሽን አገልግሎት መስጠት**<br>3.1. ከሠራተኞችና ኃላፊዎች ለሚቀርቡ የማስረጃ መግለጫ ደብዳቤ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት | 1248 | 734 | እንደቀረበው ጥያቄ የተስተናገደ | |
| | 3.2. የሠራተኞችን በዕድሜ ጡረታ በራስ ፈቃድ ስንብት ማስፈጸም | 179 | 278 | ›› | |

#### 1.3.1.4 ሌሎች ግብአቶችን ማሟላት

ለሥራ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ለማሟላት 19 ጨረታዎችን በማውጣትና በማዘጋጀት በግማሽ ዓመቱ

- 350 ዴስክ ቶፕና ላፕቶፕ ኮምፒውተር፣ 200 የባለሙያ ወንበሮች፣ ከ400 በላይ ደስታ ወረቀቶችና ሃርድ ከቨሮች፣ ፕሪንተር እና ፎቶኮፒ ማሽን እንዲሁም የንፅህና መጠበቂያ ዕቃዎችና የመሳሰሉት ግዥ ተፈፅሟል ።

## የአሠራር ስርአቶችን ስታንዳርዳይዝ ማድረግ

በ2013 በጀት ዓመት ሁሉም የሥራ ክፍሎች ወጥ በሆነ አካሄድ የየራሳቸውን የአሰራር ስርዓት/Standard Operating Procedure) እንዲያዘጋጁ እንዲሁም በተቋም ደረጃ ግልጽ የኮቺንግ እና ሜንተሪንግ ስርዓት ለመዘርጋት ትኩረት ተሰጥቶ ተሰርቷል። በዚህም መሠረት በአብዛኛዎቹ የሥራ ክፍሎች የአሰራር ስርዓት መግልጫ ዝግጅቱ ተጠናቆ ወደ ትግበራ ተሸጋግሯል።

## 1.3.2 ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማካሄድ

የኮረና ወረርሽኝ ያስከተለው ተጽእኖ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሌም እንደሚደረገው በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከውስጥ እና ከውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት ለመፍጠር የተለያዩ ውይይቶች ተካሂደዋል። በዚህም መሠረት የተደረጉት ዋና ዋና ውይይቶች መረጃ ከዚህ በታች ተመልክቷል።

### 1.3.3.1 ከውስጥ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች

ባለፉት ስድስት ወራት በሁሉም ደረጃዎች ከሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ጋር የተላዩ ውይይት ተካሂዷል። በዚህም መሠረት በኤክሲኪዩቲቭ ማኔጅመንት፣ በዘርፍ፣ በማኔጅመንት ካውንስል እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች ከሠራተኞቻቸው ጋር በተናጥል ሰፊ ውይይቶች አካሂደዋል። እነዚህ ውይይቶች ተቋማዊ መግባባትን መፍጠር የሚያስችሉ ከመሆናቸውም በላይ የውይይቱ አካል ሆነው የሚሰጡ የማነቃቂያ ስልጠናዎች የነበሩ በመሆኑ ሠራተኛውን ለማነሳሳት እና ለሥራ ያለውን ዝግጁነት ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ይታመናል።



ከዲስትሪክቶች ጋር በእቅድ አፈፃፀም ላይ የተደረገ ውይይት



### 1.3.3.2 ከውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች

ከውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ የተለያዩ ውይይቶች እና ግምገማዎች ። ይሁንና የቀጣይ አስር ዓመት የዘርፉን ዕቅድ በተመለከተ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማት፣ ከምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የሴክተር ባለድርሻ አካላት እና ከክልሎች ጋር ውይይቶች ተካሂደው የጋራ ግንዛቤ መፍጠር እና ግብአት መሰብሰብ ተችሏል።



ከወጭ  ኮንትራክተሮች ጋር የተደረገ የስራ ግምገማ



በትራንስፖርት ዘርፍ የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ዙርያ የተደረገ ውይይት

# ምዕራፍ ሁለት

2

# የተቋማዊና ስትራቴጂያዊ (ቁልፍ) ጉዳዮች አፈፃፀም

## 2.1 ከለውጥ ሥራ አመራር እና ተቋማዊ ልማት ጋር ተያይዞ የተከናወኑ ተግባራት አፈፃፀም

በለውጥ ሥራ አመራር ዙሪያ ታቅደው የሚካሄዱ የለውጥ አጀንዳዎችን በአግባቡ በመለየት የታሰበውን ዒላማ በማሳካት የመንገድ ግንባታውን ዘርፍ አፈጻጸም በተሻለ የብቃት ደረጃ ላይ እንዲያደርሱ ለማስቻል የለውጥ ሂደቱን በማቀድ፣ በማቀናጀት፣ በሁሉም ተዋናዮች ዘንድ ግንዛቤ እንዲፈጠር የማስቻል ሥራ የተከናወነ ሲሆን ስለአፈጻጸማቸው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የለውጡን ቀጣይነትና ውጤታማነት ለማረጋገጥ ሙያዊ አበርክቶ ወይም እገዛ በመስጠት የለውጥ አጀንዳዎች የመለየት፣ የማደራጀት እና የክትትልና የድገፍ ሥራ ተከናውኗል።

ኢመባ በ2013 በጀት ዓመት ከ30 በላይ አዳዲስ ኢኒሼቲቮች ወደ ጥናት እና ትግበራ እንዲገቡ አቅዶ እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ ሲሆን፣ አዲስ ወደ ጥናት እና ትግበራ እንዲገቡ የታቀዱት ከኢመባ የብቃት ሞዴል አንጻር ቀጥለው ቀርበዋል:-

## 2.2 ፖሊሲና ስትራቴጂ

በዚህ ምድብ ውስጥ የሚዘጋጁ ሰነዶች የተቋሙን ብሎም የዘርፉን አጠቃላይ አሰራር እና አመራር ሊወስኑ የሚችሉ ጉዳዮች ሲሆኑ በዚሁ አግባብ አንዳንዶቹ ሰነዶች የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ፣ ግብአት፣ የጋራ መግባባት እና ውሳኔ ሊፈልጉ ይችላሉ። በዚህ ደረጃ እየተዘጋጁ ያሉ ሰነዶች አፈፃፀም ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፣

- ✓ የመንገድ አገልግሎት ደረጃ ምደባ ጥናት /Road Functional Classification Study/ - የፕሮጀክቱ ዋና አላማ ወቅታዊ መረጃን መነሻ በሚያደርገው የተከለሰ የትራፊክ አመንጪ አካባቢዎች (Updated Trafic Generating Areas) ላይ በመመርኮዝ መንገዶችን በአገልግሎት ፋይዳቸው እና ደረጃቸው ለመመደብ የሚያስችል ስርዓትን መዘርጋት፣ ነባር መንገዶችን በዚሁ መሠረት መመደብ፣ የአዳዲስ መንገዶችን ደረጃ መመደብ፣ እንዲሁም የመንገድ ባለቤትነትና ስልጣን እና የአስተዳደር ሃላፊነትን የሚወስን ሲሆን አሁን በኢመባ ደረጃ ተጠናቋል።
- ✓ የመንገድ አዋጅ - የመንገድ አገልግሎት ደረጃ ምደባ ጥናትን እና ሌሎች ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ በመንገድ ዘርፍ ውሳኔ እና አቅጣጫ ለሚሹ ጉዳዮች የህግ ማዕቀፍ በመሆን አሁን ላይ ለሚስተዋሉ የአደረጃጀት፣ የስልጣን እና ኃላፊነት፣ የመንገድ ባለቤትነት፣ ወ.ዘ.ተ. ክፍተቶች ምላሽ የሚሰጥ ሰነድ ነው።
- ✓ ኢመባን መልሶ ማቋቋሚያ ደንብ /ERA Re-establishment Regulation/ - ዝግጅቱ ተጠናቆ ለሚመለከተው አካል/መንግስት ቀርቧል።

- ✓ የመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ - ተጠናቋል፡፡
- ✓ የአካባቢና ማህበራዊ ጉዳዮች እና የሥራ ቦታ ደህንነት ፖሊሲ ዝግጅት በማጠናቀቅ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ - ተጠናቆ ወደ ትግበራ ተሸጋግሯል፡፡
- ✓ የኢመባን የሰው ኃብት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ዝግጅት በማጠናቀቅ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ - ተዘጋጅቶ ተጠናቋል፡፡
- ✓ የተቋሙን የኮሙኒኬሽን ፖሊሲ እና ስትራቴጂን ሰነድ አፅድቆ ተግባራዊ ማድረግ - ተዘጋጅቶ ተጠናቅቋል

## 2.3 የሰው ኃይል እና አመራር

- ✓ በተጓደሉ አመራሮች ቦታ ምትክ እንዲሁም የመንገድ ጥገና ዲስትሪክቶችን ጨምሮ በተወሰኑ አካባቢዎች ሥራን ማዕከል ያደረገ የአመራር ለውጦች ተደርገዋል፣
- ✓ የሙያ ዕድገትን /career development/ ከአስገዳጅ ስልጠና ጋር ማስተሳሰር የሚያስችል ከሪኩለም እና የስልጠና ሞጁል ዝግጅት ለማካሄድ ከኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢኒስቲትዩት ጋር በጋራ እየተሰራ ይገኛል፣
- ✓ የሥራ መደቦችን በቅጥር፣ እድገት እና ዝውውር መሙላት ተችሏል፣
- ✓ በተለያየዩ ደረጀዎች ለሚገኙ ሠራተኞች እና የሥራ ኃላፊዎች ስልጠና ተሰጥቷል

የኢመባ የሥራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በሚሰሩት ሥራ ላይ ያላቸውን ተሳተትፎ እና የእርካታ ደረጃ ለማወቅ እና ክፍተቶች ከተገኙ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ እንዲሁም ጠንካራ ጎኖችን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማጎልበት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት (ERA Employees Engagement and Job satisfaction level survey) ለማድረግ የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ ተዘጋጅቶ የፓይለት ቴስት (ቅድመ ጥናት ሙከራ) ሥራ ለማከናወን ከ30 በላይ መጠይቆች በማሰራጨትና በማሰባሰብ የትንተና ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

## 2.4 ከባቢያዊ ሁኔታና ተቋም ግንባታ

የሥራ ቦታን ምቹ ከማድረግ አኳያ ሰፋፊ ሥራዎች መከናወናቸው ይታወቃል፡፡ ይሁንና የሥራ ቦታን አመቺ ማድረግ በባህሪው ቀጣይነት ያለው ሥራ በመሆኑ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በዚህም መሠረት በበጀት ዓመቱ በተቀመጠው የትኩረት አቅጣጫ መሠረት በዋና መ/ቤት ደረጃ የኦዲዮ ቪዡዋል ላይብሬሪ፣ የስቱዲዮ፣ የማኔጅመንት ስልጠና ማዕከል ግንባታና ማሻሻያ ለማድረግ የሚያስችል ዲዛይን ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ ከተቋም ግንባታ ጋር በተያያዘ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ የሚገኘው የመንገድ ምርምር ማዕከል ግንባታውን ማጠናቀቅ ነው፡፡ በዚህም መሠረት አጠቃላይ የግንባታ ሥራው 83.26 ከመቶ የደረሰ ሲሆን በበጀት ዓመቱ

ቀሪ ጊዜያት ግንባታውን በማጠናቅቀ ለማስመረቅ ታስቧል። በተመሳሳይ የመንገድ ስልጠና አካዳሚ እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ዲስትሪክቶች የዲዛይን ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።።

## 2.5 አደረጃጀት እና መዋቅር

የተቋሙን መዋቅር ማስተካከል፣ የሥራ መደቦችን የሥራ መዘርዝር ክለሳ ለማጠናቀቅ ፣ ለመሰነድ ፣ እንዲሁም ለማሠራጨት በ6 ወራት 100% ለማጠናቀቀቅ እቅድ ተይዞ 90% ማከናወን ተችሏል። በቀጣይ ቀሪ ሥራዎችን በማጠናቀቅ ለውሳኔ የሚቀርብ ይሆናል።

## 2.6 ዋና የስራ ሂደቶች

በተቋሙ የሚከናወኑ ማንኛውም የማሻሻያ ሥራዎች በዋና የተቋሙ ተግባራት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ እና በዛ ላይ መሰረታዊ ማሻሻያ ሊያደርጉ የሚችሉ ኢኒሺዬቲቮች በበጀት ዓመቱ በሁሉም ዘርፎች ትኩረት ተሰጥቶበት እየተከናወነ ይገኛል ። ከዚህ በተጨማሪ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ጥናታቸው ተጠናቆ ወደ ትግበራ የተሸጋገሩ የተለያዩ ማኑዋሎች፣ የአሰራር ማሻሻያዎች እና የጥናት ውጤቶች ትግበራ ያለበትን ደረጃ ለመገምገም የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣

- ✓ በዲዛይን፣ የኮንትራት አስተዳደር፣ የፕሮጀክት ማኔጅመንት እና የመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶችን ትግበራ ያለበትን ደረጃ ለመገምገም የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሥራ ተጀምሯል።
- ✓ የኢመባን የመሳሪዎች ጥገናና አስተዳደር ማሻሻል የሚያስችል ጥናት እየተካሄደ ነው አፈጻጸሙም **30%** ደርሷል
- ✓ Establishing a Standard Occupational Health and Safety (OHS) System. የፕሮጀክቱ ዋና አላማ በኢመባ ውስጥ የጤና ሙያ ደህንነት ስርዓትን ማጠናከር ሲሆን ግለሰብ አማካሪ ተቀጥሮ በቦታው ላይ ለባለሙያዎች ሥልጠና እና ሙያ ጤና ደህንነት መመሪያ የመጨረሻ የአደጋ ግምገማ ረቂቅ ሪፖርትና ረቂቅ ፖሊሲ ያቀረበ ሲሆን በቀጣይም በደንበኛው የሚሰጡ አስተያየቶችን በማካተት የ OHS መመሪያና ፖሊሲን ማጠናቀቅ እና የማረጋገጫ ዝርዝሮችን ማዘጋጀት ሲሆን በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጁ ሰነዶች ግብዓት እየተደረገበት ይገኛል
- ✓ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን /service standard/ የመከለስ ሥራ እየተካሄደ ነው አፈጻጸሙም **15%** ደርሷል
- ✓ የERA Image Building and Branding ጥናትን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ፕሮግራም ተቀርጾ በትግበራ ላይ ያለ ሲሆን አፈጻጸሙም **30%** ደርሷል።

- ✓ የሥራ ክፍሎች ግልጽ እና ወጥ በሆነ መልኩ መደበኛ ሥራቸውን በተገቢው መንገድ መሰነድ እና የሚስችላቸው የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (Standard Operating Procedures) 100% ለማጠናቀቅ ታቅዶ 90% ሥራ ተከናውኗል
- ✓ ERA Project Handover Guideline -- የፕሮጀክቱ ዋና አላማ ማንኛውም የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች የፕሮጀክት ባለድርሻ አካላት (ኢመባ፣ ተቋራጭ እና አማካሪዎች) በተገቢው ጊዜ መንገድ እንዲወሰዱ እና እንዲታቀዱ ለማድረግ የታቀዱትን ሙሉ በሙሉ በተገቢው መረጃና በታቀደ ልክ በማዋቀር አስፈላጊው ስራ ተሰርቷል
- ✓ የኢመባ ዕውቀት አስተዳደር ሥርዓት/knowledge Management System/ ዝርጋታ፤- የኢመባ ዕውቀት አስተዳደር ስርዓት ለመዘርጋት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ለዓለም ባንክ ተልኮ ግብዓት ተደርጎበት የመጨረሻው ቅርጽ ዓለም ባንክ የአማካሪውን ቅጥር ለመፈጸም በሂደት ላይ ይገኛል፡፡
- ✓ የኢመባ ደንበኞች እና ባለድርሻ አካላት የእርካታ ደረጃ ጥናት የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ የኢመባን ባለድርሻ አካላት ደረጃ ለማወቅ እና የመጀመሪያ መሠረት (ቤዝ ላይን) ማስቀመጥ ሲሆን በአማካሪ ድርጅት እየተጠና የሚገኝ ሲሆን ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ፡-
  - በሁሉም የኢመባ ዲስትሪክቶች እና ኔትዎርክ ዳይሬክቶሬቶች መረጃ ለመሰብሰብ የተመለመሉ የኢመባ ባለሙያዎች በአማካሪ ድርጅቱ አማካኝነት የመረጃ አሰባሰብ ስልጠና እና የሙከራ መረጃ አሰባሰብ ተከናውኗል
  - መረጃውን የመሰብሰብ ሁኔታ በሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከተጠቃሚ የሚሰበሰበው መረጃ 90 በመቶ በላይ ተሰብስቧል፤ የኪይ ኢንፎርማንት ኢንተርቪው እና ደንበኞች እና ባለድርሻ አካላት መረጃ መሰብሰብም በሂደት ላይ ነው፡፡

## 2.7 የኢመባ ዲጂታይዜሽን እና ቴክኖሎጂ

የኢመባን የሲስተም እና ሁለንተናዊ የአይቲ አቅም ከማሳደግ አኳያ በ6 ወራት ተግባራዊ የተደረጉ ሥራዎች የእንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ✓ በዓለም ባንክ ድጋፍ የሚደረገውን የመጀመሪያውን ምዕራፍ የአይቲ አቅም (ዳታሴንተር) ግንባታ ፕሮጀክት ግዥ ተጠናቆ አሸናፊው ድርጅት ወደ ሥራ ገብቷል፤





እስካሁን ባለው አፈጻጸም፣ ዝርዝር የመስክ ምልከታ ተካሂዷል፣ ረቂቅ የዲዛይን ጥናት ቀርቧል፣ አስተያየት ተሰጥቶበታል፣ የሲቪል ወርክ ሥራዎች እየተጠናቀቁ ነው ከውጭ የሚገዙ ዕቃዎች እየተጓጓዙ ነው፡፡



- ✓ በውስጥ አቅም የበለፀገው የኢፋይሊንግን ስርአት ሶፍትዌር የሙከራ ትግበራ ተጠናቆ በዋናው መ/ቤት ደረጃ በሁሉም የሥራ ክፍሎች ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል
- ✓ የተቋሙን የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት የሚቀንሱ ሥራዎች ከመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ጋር በጋራ እየተሠራ ነው
- ✓ የዲጂታል ሳይኔጅ አጠቃቀም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የመደበኛ ሥራዎች አፈፃፀም

3

## 3.1 የቅድመ ግንባታ ሥራዎች አፈጻጸም

### 3.1.1 የምህንድስና ግዥ አፈፃፀም

የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በ2013 በጀት ዓመት በአጠቃላይ የአዲስ ግንባታ እና ማሻሻል ፕሮጀክቶችን ጨረታ ሂደት ማከናወን (117 ፕሮጀክት) ፣ የግንባታ ተቆጣጣሪ መሐንዲስ ቀጠራ ጨረታ ሂደት ማከናወን (153 ፕሮጀክት)፣ የዲዛይን አማካሪ ግዥ ሂደት ማከናወን (48 ፕሮጀክት)፣ የ 30 ፕሮጀክቶች የቴክኒክ ድጋፍ ግዥ ማከናወን፣ ሁለት የማማከር ሥራ ያልሆኑ እና ሌሎች ፕሮጀክቶች ግዥ ፣ የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ግዥ ማከናወን (44 ፕሮጀክት)፣ የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ተቆጣጣሪ መሐንዲስ ግዥ ማከናወን (49 ፕሮጀክት) እንዲሁም የመንገድ ደህንነት ፕሮጀክቶች ግዥ ማከናወን (5 ፕሮጀክት) ለማከናወን የግዥ ዕቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የ6 ወራት አፈፃፀም ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

#### 3.1.1.1 የአዲስ ግንባታ እና የደረጃ ማሻሻል ፕሮጀክቶችን ጨረታ ሂደት ማከናወን

- ✓ የጨረታ ሂደታቸዉ በ2012 በጀት ዓመት የተጀመሩ 30 ፕሮጀክቶችን የግዥ ሂደት ለማጠናቀቅ ታቅዶ 22 ፕሮጀክቶችን የተፈረሙ ሲሆን 2 ፕሮጀክቶች 65% የፋይናንሻል ግምገማቸው የተጠናቀቀ፣ 6 ፕሮጀክቶች 52% የቴክኒካል ግምገማ የተከናወነላቸው ናቸው፡፡
- ✓ የ46 ፕሮጀክቶችን የጨረታ ሂደት ለማስጀመር ታቅዶ የ 39 ፕሮጀክቶችን የጨረታ ሂደት ማስጀመር የተቻለ ሲሆን ቀሪዎቹ 7 ፕሮጀክቶች ዲዛይን ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

#### 3.1.1.2 የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶችን ጨረታ ሂደት ማከናወን

- ✓ የ12 ፕሮጀክቶችን የግዥ ሂደት ለማጠናቀቅ ታቅዶ 6 ፕሮጀክቶች የተፈረሙ ሲሆን 2 ፕሮጀክቶች 56% የቴክኒካል ግምገማ የተጠናቀቀ፣ 4 ፕሮጀክቶች 38% ጨረታ ወቶላቸው አየር ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡
- ✓ የ19 ፕሮጀክቶችን የጨረታ ሂደት ለማስጀመር ታቅዶ በዚሁ መሠረት የ19 ፕሮጀክቶችን የጨረታ ሂደት ተጀምሯል፡፡

#### 3.1.1.3 የድልድይ ግንባታ ግዥ

- ✓ 1 ፕሮጀክት የድልድይ ግንባታ ግዥ ለማከናወን ታቅዶ የፕሮጀክቱ ግዥ ተጠናቋል፡፡
- ✓ 5 ድልድይ ግንባታ ፕሮጀክቶችን የጨረታ ሂደት ለማስጀመር ታቅዶ 5 ቱንም ማስጀመር ተችሏል፡፡

#### 3.1.1.4 የግንባታ ተቆጣጣሪ አማካሪዎች ቀጠራ ጨረታ ሂደት ማከናወን

- ✓ ለ77 የግንባታ ፕሮጀክቶች የተቆጣጣሪ አማካሪዎች ቀጠራ የጨረታ ሂደት ለማከናወን ታቅዶ ለ29 ፕሮጀክቶች የተቆጣጣሪ አማካሪ መቅጠርና ማስፈረም የተቻለ ሲሆን ቀሪዎቹ 48 ፕሮጀክቶች ፋይናንሻልና ቴክኒካል ግምገማ ላይ ይገኛሉ ።
- ✓ ለ21 የግንባታ ፕሮጀክቶች የተቆጣጣሪ አማካሪዎ ቀጠራ የጨረታ ሂደት ለማስጀመር ታቅዶ ለ21 ፕሮጀክቶችን የጨራታ ሂደት ማስጀመር ተችሏል፡፡

#### 3.1.1.5 ዲዛይን የሚሰራ አማካሪ ቀጠራ የጨረታ ሂደት ማከናወን

- ✓ የጨራታ ሂደታቸዉ በ2012 በጀት ዓመት የተጀመሩ የ 47 ፕሮጀክቶችን የዲዛይን አማካሪ የጨረታ ሂደት ለማስፈረም ታቅዶ 32 ፕሮጀክቶችን ማስፈረም የተቻለ ሲሆን ቀሪ 14 ፕሮጀክቶችን 62% የቴክኒካል ግምገማ እና 1 ፕሮጀክት 20% በEOI ግምገማ ላይ የሚገኙ /Under EOI Assesment Period/ላይ ይገኛሉ፡፡
- ✓ ለ1 ፕሮጀክቶችን የዲዛይን አማካሪ የጨረታ ሂደት ለማስጀመር ታቅዶ የ 1 ፕሮጀክቶችን የጨረታ ሂደት ማስጀመር ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ የበርካታ ፕሮጀክቶች ግዥ እንዲፈጸም የሚጠበቅ ከመሆኑ አኳያ ከወዲሁ ይህን መሸከም የሚችል ገበያ ስለመኖሩ መነሻ ጥናት እና ትንተና /Market Assessment/ በማካሄድ የመፍትሄ እርምጃዎች ተመላክተዋል፡፡

### 3.1.2 የዲዛይን ሥራዎች አፈጻጸም

### 3.1.3 የዲዛይን ሥራዎች አፈጻጸም

ከዲዛይን ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ባለፈው በጀት አመት ተጀምሮ ሳይጠናቀቁ የቆዩትን ጨምሮ በ2013 በጀት ዓመት ከተያዙት 93 ፕሮጀክቶችና በቅርብ የተጨመሩትን 3 ፕሮጀክቶች ጨምሮ ባጠቃላይ 96 ፕሮጀክቶችን ዲዛይን ለማሰራት የታቀደ ሲሆን እስከ 6 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ 56 ፕሮጀክቶችን ዲዛይን እያስተዳደረ ነው :-

- ✓ ከ56 የዲዛይን ፕሮጀክቶች ወስጥ 39 ፕሮጀክቶችን ለምህንድስና ግዥ ለማስተላለፍ ታቅዶ 29 (74%) ፕሮጀክቶችን ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በ6 ወራት በዲዛይን ክፍል ሊከናወኑ ከታቀዱ 77 ፕሮጀክቶች ወስጥ የ29 ፕሮጀክቶችን ዲዛይን ስራ አጠናቆ አጠቃላይ የእቅዱን **83%** ማከናወን ተችሏል፡፡

**በ6 ወራት የዲዛይን ስራቸው የተጠናቀቁ 29 ፕሮጀክቶች**

1. ቶንጎ - አሶሳ
2. ሱፒ - ዳርሙ - ላሎክሌ
3. አርሲ ሮቤ - አጋርፋ -አሊ ሎት 2 ፡ አርሲ ሮቤ -ዋቢ ሪቨር ብሪጅ
4. ሰቃ-አትናጎ-አልጌ-ሰዮ-ሸነን-ጉደር
5. መቱ ባይፓስ
6. ቱሉቦሎ-ቡሳ-ጊንጪ
7. ጂግጂጋ ባይፓስ
8. ኮምቦልቻ-ባይፓስ
9. ደሴ-ባይፓስ
10. ቁጭ አየሁ ዚገም ቻግኒ
11. የድልድይ ስራ በጅማ ዲስትሪክት ጥቅል
12. ነጆ-ጃረሶ-በጊ-ያዮ መንገድ ፕሮጀክት፤ ሎት1፡ነጆ- ኬ.ሜ. 65 እና ሎት2፡ኬ.ሜ. 65- ያዮ
13. ቡሌሆራ - ሻኪሶ - ክብረመንግስት ሎት 1፡ ክብረመንግስት - ቡሌ ቀሮ
14. አላማጣ - ጭለና - መረዋ - ፀፀር - ዴላ፡ ዕጣ 1፡ አላማጣ - ኪሜ 65
15. ቦኖሻ - አቻሞ
16. ራማ - ግረሁሰናይ
17. ዴሎሰርቦ_ጃራ_ሸክሁሰን ቅድመ የዲዛይን ጥናት
18. ላሊበላ - ኩልመስክ-ሙጃ- ቆቦ ሎት 2
19. ዶዶላ - ክብረመንግሥት
20. አላባ -አንጋጫ -ዋጦ እና ዶምቦያ- ዱራሜ ስፐር መንገድ ፕሮጀክት
21. ዳራማሎ- ኦቶሎ መንገድ ፕሮጀክት
22. ፊልቱ-ዶሎ ኦዶ-ዶሎ ባይ ዝርዝር የዲዛይን ጥናት
23. አጋሮ - ጌራ - መዳአቦ
24. ሞጆ_ ሃዋሳ ITS ፕሮጀክት
25. ኝኛንግ- ኦንጎግ (ጂካዎ- ቶሃ)
26. ጉሊሶ - ጪላ - ቀንዲላ - ቤጊ፡ ዕጣ 1፡ ጉሊሶ- ኪሜ 70
27. ደብረ ማርቆስ - ባህርዳር የመንገድ ማሻሻያ እና የእንጅባራ ከተማ ማስፋፊያ
28. ጎግ-ጆር-አኮቦ
29. ዳንግላ - ጃዊ

### 3.1.4 የቅድመ ግንባታ የወሰን ማስከበር ሥራዎች አፈጻጸም

በበጀት ዓመቱ 6 ወራት የመንገድ ወሰን እና መብት ከማስከበር ጋር የተያያዙ ሥራዎች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲከናወኑ ከማድረግ አኳያ የተሰሩ ሥራዎች :-

ሠንጠረዥ 4፡ የወሰን ማስከበር ስራዎች

| ተ.ቁ | ተግባራት በዝርዝር | ዕቅድ | ክንውን | ክንውን በትንታኔ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በመንገድ ክልል ውስጥ የገቡ ንብረቶች እና የአገልግሎት መስመሮች መንገዱ ለሥራ ተቋራጮች ከመሰጠቱ በፊት ንብረቶቹ ተገምተውና ክፍያ ተፈጽሞ ከመንገድ ወሰን ውስጥ እንዲነሱ ማድረግ (ለ19 መንገዶች/255 ክ.ሜ)<br>**የግምት ሥራ ተጠናቆ የካሳ ክፍያ ለመፈጸም በሂደት ላይ ያለ፡**<br>- ሰገግ- ገርቦ፣ ሰዮ - ሸነን - ጉደር (4.7 ኪ. ሜ) እና ጎግ - ጆር - አኮቦ በ2 ከተሞች ላይ 2.39 ኪ. ሜ<br>**የካሳ ግምት ሥራ እየተከናወነ የሚገኝ።**<br>- ቁጭ - አየሁ - ዝግም 21 ኪ.ሜ እና ጅግጅጋ ማሳለጫ 6.86 ኪ ሜ | 81 | 99.5 | -ዩአለ (ገርቦ) ደነን ፕሮጀክት (82 ኪ.ሜ) ፣<br>-አላባ - አንጋጫ - ዋቶ (10.5 ኪ. ሜ) ፣<br>-ቦኖሻ - አጫሞ (7 ኪ.ሜ) ንብረት ተነስቷል። |
| 2 | ከዚህ በፊት መድረክ ባልተደረገባቸው ክልሎች ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ አፋር እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ላይ የጋራ መድረክ ማመቻቸት | 2 | 3 | በአማራ፣ በሶማሌ እና በሲዳማ ብሔራዊ ክልሎችጋር የጋራ መድረክ ተካሂዷል። |
| 3 | ከመንገድ ወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ የአገልግሎት መስጫ መስመሮች/ንብረቶች ከመንገድ ወሰን ክልል ውስጥ በወቅቱ የሚነሱበትን ሁኔታ ላይ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር የእቅድ ክንውን ግምገማ መድረኮች እንዲመቻች | 1 | 1 | የእቅድ ክንውን ግምገማው ተካሂዷል።<br>በጋራ እቅድ ተዘጋጅቷል |
| 4 | ከመንገድ ወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ ለሚመጡ ችግሮች ከተቀናጀ የመሰረተ ልማቶች ኤጀንሲ ጋር በመሆን የጋራ መድረክ ማዘጋጀት | 2 | 1 | በአዳማ ከተማ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር የ2 ቀናት ውይይት ተደርጓል |
| 5 | በመንገድ ወሰን ማስከበር ሞደርናይዜሽን እና በካሳ ክፍያ እና መልሶ ማቋቋሚያ አወጅ ማስፈጻሚያ ደንብ ቁጥር 472/2012 ላይ ለሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት | 1 | 1 | በአጠቃላይ በ2 ዙር ለ140 ሃላፊዎችና ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል |

## የ2013 በጀት ዓመት የእስካሁን የመንገድ ተነሽዎች የካሳ ክፍያ አፈጻጸም

**የተከፈለ**

| | |
|---|---|
| በኮሜርሻል ኖሚኒስ ለተከፈለ መተኪያ | 3,133,553,101.99 |
| የተቋማት ንብረት ግምት (Utility) | 342,168,890.24 |
| የአገልግሎት ክፍያ | 152,022,299.09 |
| ድምር | **3,627,744,291.32** |

**በሂደት ላይ የሚገኝ**

| | |
|---|---|
| ፋይናንስ የደረሰ | 193.69 ሚ. |
| በመጣራት ሂደት ላይ ያለ | 142.00 ሚ. |
| ለኮሜርሻል ኖሚኒስ ለክፍያ የተላከ | 171.00 ሚ. |
| ድምር | **506.69 ሚ** |

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት በመንገዶች ግንባታ ምክንያት ለሚነሱ ንብረቶች እና የአገልግሎት መስመሮች የሚከፈለው የገንዘብ መጠን ከ4 ቢሊዬን ብር በላይ መድረሱ የወሰን ማስከበር እና ካሳ ክፍያ ሥራን ውስብስብነት ከማሳየት ባለፈ መንግስት ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መመርመር እንዳለበት የሚያመለክት ነው። በተለይም አዲስ የጸደቀው አዋጅ የሚያስከትለውን ከፍተኛ የበጀት ጫና ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የጉዳዩን አሳሳቢነት እንዲረዱት ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

### በመንገድ ወሰን ማስከበርና ከካሳ ክፍያ ጋር በተያያዘ ከማህበረሰቡ ለሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት

- ✓ የሞጆ - መቂ መንገድ ፕሮጀክት ላይ 14 ቤቶች ካሳ ክፍያ ግምት ጥያቄ ተነስቶ ካሳ ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ተደርጓል።
- ✓ አርሲ - ነገሌ - ሃዋሳ ላይ የመቃብር ማረፊያ ቦታ እና ወደ ግለሰብ ቤት መግቢያ በር ላይ በተነሳ የካሳ ይከፈለኝ ጥያቄ ላይ ካሳ ክፍያ እንዲከፈል ተደርጎ ምላሽ አግኝቷል ።
- ✓ መተማ - አብርሃጅራ መንገድ ፕሮጀክት ላይ ለረጅም ጊዜ የቆየ የካሳ ክፍያ ቅሬታ ተፈቷል።
- ✓ አዘዞ - ጎንደር ላይ ከውሃ መስመር ጋር በተያያዘ የተነሳውን ቅሬታ እና የኳሪ ሳይት ክፍያን ዘላቂ ይደረግልን ጥያቄ መፍታት ተችሏል።
- ✓ አርበረከቴ - ገለምሶ ላይ ከቦሮ ፒትና ኳሪ ሳይት ዘላቂ ክፍያ እና በመንገድ ስራው ምክኒያት ንብረታቸው ጉዳት የደረሰባቸውን የካሳ ክፍያ ጥያቄዎች ተፈተዋል።

## 3.2 የግንባታ ሥራዎች አፈፃፀም

### 3.2.1 የፕሮጀክቶች የፊዚካል አፈጻጸም


በ2013 በጀት ዓመት የ6 ወራት የግንባታ ፕሮጀክቶች የፊዚካል ስራዎች ዕቅድ አፈፃፀም በነባር መንገዶች ማጠናከር 12 ኪ. ሜ ዕቅድ ተይዞ 14 ኪ.ሜ ፤ በነባር መንገዶች ደረጃ ማሻሻል 169 ኪ.ሜ ታቅዶ 139 ኪ.ሜ፤ የአዳዲስ መንገዶች እና የፍጥነት መንገዶች ግንባታ 437 ኪ.ሜ ታቅዶ 332 ኪ.ሜ የተከናወነ ሲሆን ከእቅዱ አኳያ አጠቃላይ አፈጻጸሙ 78 በመቶ ሆኗል።

ሠንጠረዥ 5: - የ6 ወራት የግንባታ እና ከባድ ጥገና አፈፃፀም

| ተ.ቁ | ንዑስ ተግባር | መለኪያ | የ2013 በጀት ዓመት እቅድ | የ6 ወራት | | | የዓመቱ ቀሪ ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | % | |
| **1** | **የመንገዶች ግንባታ፣ ማጠናከርና ማሻሻል** | | | | | | |
| 1.1 | ነባር መንገዶች ማጠናከር | ኪ. ሜ | 38 | 12 | 14 | 113 | 24 |
| 1.2 | የነባር መንገዶች ደረጃ ማሻሻል | “ | 455 | 169 | 139 | 82 | 316 |
| 1.3 | አዲስ መንገዶች ግንባታና የፍጥነት መንገድ | “ | 1226 | 437 | 332 | 76 | 894 |
| | **የግንባታ ሥራዎች ድምር** | | **1719** | **619** | **485** | **78** | **1234** |
| | **የመንገደች ከባድ ጥገና** | ኪ. ሜ | 844 | 307 | 157 | 51 | 687 |
| | **የግንባታ ሥራዎች ከባድ ጥገና ድምር** | | **2563** | **925** | **641** | **69** | **1921** |

**ማስታወሻ ፡ በጦርነቱ ምክንያት ሥራ ያቆሙ 21 ፕሮጀክቶች አልተካተቱም**

**ምስል 1፡-የመንገዶች ግንባታ እና ከባድ ጥገና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም**



### 3.2.2 የፕሮጀክቶች አፈፃፀም - በሃገር ውስጥ እና በውጭ ሃገር ተቋራጭ

ተቋራጮችን በተመለከተ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የአገር ውስጥና የውጭ ተቋራጮችን በመለየት የአፈፃፀም ግምገማ በየጊዜው እየተካሄደ ነው፡፡ የ2013 በጀት የ6 ወራት የተቋራጮች አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥች 6 ፡- በሃገር ውስጥ እና በወጭ ሃገር ተቋራጭ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም (በ.ኪ.ሜ)

| ተቋራጭ | | የኮንትራክተሮች ብዛት | የፕሮጀክት ብዛት | ፕሮጀክቶቹ ርዝመት | የ6 ወራት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | እቅድ | ክንዉን | መቶኛ |
| የዉጭ ሀገር ተቋራጭ | | 37 | 91 | 6,600 | 319 | 284 | 89 |
| የሃገር ውስጥ ተቋራጮች | ነባር | 22 | 102 | 6,325 | 329 | 200 | 61 |
| | አዲስ | 23 | 73 | 5,349 | 277 | 157 | 57 |
| ንዑስ ድምር | | 45 | 175 | 11,675 | 606 | 357 | 59 |
| **አጠቃላይ ድምር** | | **82** | **266** | **18,274** | **925** | **641** | **69** |

በ2013 በጀት ዓመት 6 ወራት በ45 የሀገር ዉስጥ እና 37 የዉጪ ሀገር ተቋራጮችን በማሳተፍ 266 ፕሮጀክቶችን ጠቅላላ ርዝመታቸዉ 18,274 ኪ.ሜ በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡ በዉጭ ሀገር ተቋራጭ የተያዙ የፕሮጀክቶች ብዛት 91 ሲሆኑ ጠቅላላ ርዝመታቸዉ 6,600 ኪ.ሜ ነዉ፡፡ በ2013 በጀት ዓመት 6 ወራት እቅድ የተያዘላቸዉ የዉጭ ሀገር ተቋራጮች የመንገድ ርዝመት 319 ኪ. ሜ ሲሆን አፈፃፀማቸዉ 284 ኪ. ሜ (89 በመቶ) ሆኗል፡፡

የሀገር ዉስጥ ተቋራጮችን ስንመለከት ነባርና አዲስ ተብለዉ በሁለት የተከፈሉ ሲሆን፤ ነባር ኮንትራክተሮች የያዙት የፕሮጀክት ብዛት 102 ሲሆን ጠቅላላ ርዝመታቸዉ 6,325 ኪ.ሜ ነዉ፡፡ በአዲስ ተቋራጭ የተያዙት ፕሮጀክቶች ብዛት 73 ሲሆን ጠቅላላ ርዝመታቸዉ 5,349 ኪ.ሜ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ነባር ተቋራጮች በ2013 በጀት 6 ወራት አንዲያከናዉኑ የተያዘላቸዉ እቅድ 329 ኪ.ሜ ሲሆን ያከናወኑት 200 ኪ.ሜ (61 በመቶ) ነዉ፡፡ በአንፃሩ የአዳዲስ ኮንትራክተሮችን አፈፃፀም የተያዘላቸው ዕቅድ 277 ኪ.ሜ ሲሆን ክንዉናቸዉ 157 ኪ.ሜ (57 በመቶ) ነዉ፡፡ በአጠቃላይ የሃገር ውስጥ ኮንትራክተሮች አፈፃፀም (59 በመቶ) ዝቅ ያለ ሲሆን ለዚህም በአንዳንድ አካባቢዎች ያለው የፀጥታ ችግር ፣ የግብዓትና የማቴሪያል እጥረት ፣ የኮንትራክተር አቅም ማነስና የገንዘብ ፍሰት ችግር እንዲሁም የካሳ ክፍያ መዘግት ፣ የROW ችግር ፣ COVID-19 ምክንያት ተጓዳኝ የጤና ችግር ያለባቸው የሰረተኛ ቅነሳ በመደረጉ ዋና ዋና ምክኒያቶች ናቸው፡፡

**ሠንጠረዥ 7፡- የውጭ ሃገር ተቋራጮች የሥራ አፈጻጸም**

| ተ.ቁ | ተቋራጭ | የፕሮጀክት ብዛት | ርዝመት | የ6 ወራት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | % |
| 1 | Al Asab | 2 | 103 | 8 | 1 | 13 |
| 2 | Arab Contractors | 1 | 74 | | 3 | ++ |
| 3 | Beijing urban Constraction | 3 | 218 | 21 | 12 | 60 |
| 4 | China Communication Constraction Campany (CCCC) | 12 | 769 | 50 | 78 | 156 |
| 5 | CGC Overseas construction group | 6 | 515 | 9 | 2 | 24 |
| 6 | China First Highway | 1 | 100 | 8 | 3 | 43 |
| 7 | China gezhouba group | 2 | 130 | 11 | 10 | 92 |
| 8 | China MCC 17 | 1 | 92 | | | |
| 9 | China Railway no.3 | 5 | 368 | 19 | 18 | 96 |
| 10 | China Railway no.8 | 1 | 65 | 3 | 2 | 67 |
| 11 | China railway no.7 | 9 | 662 | 24 | 20 | 83 |
| 12 | China state construction engineering corporation | 3 | 206 | 12 | 5 | 39 |
| 13 | China tiesiju civil engneering | 4 | 282 | 9 | 4 | 45 |
| 14 | China Railway 14 | 1 | 88 | 1 | 0 | 35 |
| 15 | chaina railway 21st | 2 | 156 | 10 | 7 | 67 |
| 16 | China civil engineering construction corporation | 2 | 121 | 4 | 10 | 272 |
| 17 | China water and electric | 1 | 51 | | | |
| 18 | Cholgqing International Corporation | 2 | 169 | 2 | | |
| 19 | China wuyi | 4 | 322 | 22 | 16 | 71 |
| 20 | CRCC 21 | 1 | 103 | 5 | 4 | 77 |
| 21 | Daewoo Eng. & Cons. Co.LTD (DE&Co.Ltd) | 1 | 37 | 2 | 3 | 160 |
| 22 | Dogusan insaat Tic.A.S and rahab and sons plc (jv) | 1 | 88 | 1 | 3 | 30 |
| 23 | Hawk | 1 | 61 | 1 | | |
| 24 | Hobi Constraction | 2 | 132 | 11 | 13 | 119 |
| 25 | Hunyadi dev't company | 1 | 140 | 8 | 4 | 58 |
| 26 | Hunan Hunda | 2 | 156 | 9 | 9 | 110 |
| 27 | Investory prockt | 1 | 58 | 4 | 3 | 65 |
| 28 | Jiangxi Water and Hydropower Construction | 2 | 120 | 4 | 1 | 15 |
| 29 | JMC projects | 1 | 88 | 5 | 11 | 237 |
| 30 | NKH construction | 1 | 74 | 8 | 10 | 125 |
| 31 | Ningxia communicaton constraction | 1 | 77 | 3 | 3 | 95 |
| 32 | SBI International Holding AG (SBIIHAG) | 1 | 57 | 6 | 3 | 50 |
| 33 | Shandong highway | 3 | 245 | 13 | 4 | 32 |
| 34 | Sinohydro | 4 | 312 | 6 | 5 | 77 |
| 35 | UTE Elsamex | 1 | 64 | 4 | 4 | 97 |
| 36 | zhejiang bayong highway | 1 | 35 | 2 | 1 | 33 |
| 37 | Zhongmei engineering, china | 4 | 263 | 18 | 14 | 79 |
| | **ድምር** | **91** | **6600** | **319** | **284** | **89** |


ሠንጠረዥ 8፡ የሃገር ውስጥ ተቋራጮች የሥራ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | ተቋራጭ | የፕሮጀክት ብዛት | ርዝመት | የ6 ወራት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | % |
| | **ነባር ተቋራጭ** | | | | | |
| 1 | Afro Tsion | 4 | 191 | 16 | 5 | 33 |
| 2 | Akir | 1 | 62 | | | |
| 3 | Alemayehu Ketema | 2 | 141 | 7 | 3 | 50 |
| 4 | Aser Construction plc | 2 | 62 | 10 | 8 | 81 |
| 5 | Defense Construction | 10 | 747 | 40 | 10 | 26 |
| 6 | Diriba Defersha | 2 | 45 | 3 | 3 | 91 |
| 7 | Gemshu beyene construction PLC | 5 | 360 | 13 | 9 | 69 |
| 8 | Enyi construction | 1 | 69 | 6 | 3 | 54 |
| 9 | Ethiopian Constraction Works Corporation | 14 | 679 | 43 | 18 | 43 |
| 10 | Fal Trading | 3 | 217 | 8 | 8 | 98 |
| 11 | Macro General | 3 | 322 | 19 | 15 | 79 |
| 12 | Markan trading | 3 | 115 | 13 | 8 | 63 |
| 13 | Melcon Construction | 4 | 179 | 9 | 7 | 83 |
| 14 | Mengesha Abera | 1 | 50 | | | |
| 15 | Powercon plc | 4 | 340 | 50 | 20 | 41 |
| 16 | Rama construction | 3 | 131 | 13 | 17 | 128 |
| 17 | Satcon construction | 5 | 387 | 5 | 1 | 15 |
| 18 | Sunshine construction plc | 5 | 343 | 18 | 15 | 84 |
| 19 | Sur construction Plc | 12 | 899 | 28 | 30 | 110 |
| 20 | Tekleberhan Ambaye | 5 | 203 | 2 | 0.3 | 2 |
| 21 | Yencomad construction | 6 | 425 | 14 | 11 | 79 |
| 22 | Yotek construction | 7 | 358 | 14 | 7 | 51 |
| | ንዑስ ድምር | 102 | 6325 | 329 | 200 | 61 |
| | አዲስ ተቋራጭ | | | | | |
| 1 | Afework Gidey | 2 | 230 | 28 | 4 | 16 |
| 2 | Amhara road con. | 4 | 313 | 21 | 16 | 75 |
| 3 | Bermog construction | 1 | 60 | | | |
| 4 | Bridge Construction | 1 | 28 | 2 | 1 | 32 |
| 5 | Beaeka general business | 1 | 110 | | 5 | ++ |
| 6 | Cross- land construction | 3 | 213 | 7 | 14 | 197 |
| 7 | Dano | 1 | 36 | | | |
| 8 | Eshetu Lemma | 1 | 31 | 2 | 1 | 41 |
| 9 | Fasil tsegahana | 1 | 62 | 6 | 0.3 | 6 |
| 10 | Kiflom Gebrehiwot GC. | 1 | 27 | | | |
| 11 | oromia road con. | 3 | 114 | 10 | | |
| 12 | Orchid business group | 2 | 140 | 4 | 2 | 41 |
| 13 | Samson Chernet | 3 | 265 | 13 | 6 | 46 |
| 14 | Senan Construction | 1 | 36 | 5 | 3 | 63 |
| 15 | Sylem Construction | 1 | 271 | 9 | 2 | 20 |
| 16 | yonab constraction | 1 | 143 | 12 | 11 | 88 |
| 17 | Yosef Teketel | 2 | 107 | 16 | 19 | 120 |
| 18 | Zeluel Yohannes | 1 | 5 | 1 | 1 | 88 |

| ተ.ቁ | ተቋራጭ | የፕሮጀክት ብዛት | ርዝመት | የ6 ወራት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | % |
| 19 | Owen force | 17 | 1427 | 113 | 71 | 63 |
| 20 | Welabu constraction | 2 | 132 | | | |
| 21 | DMC Constraction | 2 | 132 | | | |
| 22 | Kibish constraction. | 1 | 62 | | | |
| 23 | Others(Procrument) | 21 | 1408 | 29 | 2 | 6 |
| | ንዑስ ድምር | 73 | 5349 | 277 | 157 | 57 |
| | ጠቅላላ ድምር | 175 | 11675 | 606 | 357 | 59 |

### 3.2.3 የፕሮጀክቶች አፈጻጸም - በአስፈጻሚ ዳይሬክቶሬት

ምስል 2፦ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም በዳይሬክቶሬት **(በመቶኛ)**




የ2013 በጀት ዓመት የ6 ወራት አፈፃፀም በሚያስተዳድሩት ዳይሬክቶሬቶች ሲታይ የምስራቅ ሪጅን ከፍተኛ አፈፃፀም ያሳየ ሲሆን ማዕከላዊ፣ ደቡብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን እና የፍጥነት መንገድ መካከለኛ አፈፃፀም ያሳዩ ሲሆን አጠቃላይ አፈፃፀሙ 78 በመቶ ሆኗል፡፡


### 3.2.4 የፕሮጀክቶች አፈፃፀም - በፋይናንስ ምንጭ

ለፌደራል መንገዶች የ6 ወራት የፊዚካል አፈፃፀም በፋይናንስ ምንጮች በምንመለከትበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ በመንግስት ወጪ እንዲሰራ በዕቅድ የተያዘው 947.2 ኪ. ሜ ሲሆን አፈጻጸሙ 587.4 ኪ. ሜ (62 በመቶ) ሲሆን በልማት አጋሮች ወጪ እንዲሰራ የታቀደው 66 ኪ.ሜ ሲሆን 54 ኪ.ሜ ክንውን (82 በመቶ) ተመዝግቧል፡፡ ከእነዚህ የልማት አጋሮች ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ የሚይዙት በአፍሪካ ልማት ባንክ፣ በአለም ባንክ፣ ኮሪያ ፣ቻይና እና ባዲያ እና ኦፊድ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 9:-በ6 ወራት በመንግስት እና የበልማት አጋሮች እየተካሄዱ ያሉ ፕሮጀክቶች የፊዚካል ስራዎች አፈፃፀም (በኪ.ሜ)

| ተ.ቁ. | ፋይናንሰር | ዕቅድ | ክንውን | መቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከመንግስት | 859.4 | 587.4 | 68 |
| | **ድምር** | **859.4** | **587.4** | **68** |
| 2 | አለም ባንክ | 8.3 | 13.3 | 161 |
| 3 | የአፍሪካ ልማት ባንክ | 22 | 22.5 | 102 |
| 4 | ኮሪያ | 13.3 | 7.2 | 55 |
| 5 | ቻይና | 5 | 2.6 | 51 |
| 7 | ባዳያ እና ኦፊድ | 5.8 | 3.1 | 54 |
| 8 | አቡዳቢ ፣ ባዲያ እና ሳውዲ ፈንድ | 6 | 4.5 | 74 |
| 9 | ሳውዲ ባዲያ እና ኦፊድ | 5.5 | 0.8 | 15 |
| | **ድምር** | **66** | **54** | **82** |
| | **አጠቃላይ ድምር** | **925** | **641** | **69** |

**ምስል 3፡- የልማት አጋሮች ድርሻ በመቶኛ**




**በ6 ወራት እቅድ ከተያዘላቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ በመንግስት ፋይናንስ የሚደረጉ 92 በመቶ ድርሻ ሲይዙ በልማት አጋር ደግሞ 8 በመቶ ነው፡፡**

### 3.2.5 አፈፃፀሙ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር

በ2013 በጀት ዓመት ከተያዘው እቅድ አንፃር በመንገዶች ግንባታ፣ ማጠናከርና ማሻሻል እንዲሁም መንገዶች ጥገና አፈፃፀም 78 በመቶ ነው፡፡ ከ2012 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ሲሆን ይህም በሃገራችን ከተከሰተው የፀጥታ ችግር እና በአለም አቀፍ ደረጃ ከተከሰተው የኮቪድ 19 ተፅዕኖ አንፃር ስራዎችን በቁርጠኝነት ለማከናወን የተሄደበትን አመርቂ ዝግጁነት ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 10:- የግንባታ ሥራዎች የ2012 እና 2013 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመትአፈፃፀም ንፅፅር

| ተ.ቁ | የስራ ዓይነት | የ2012 በጀት ዓመት የ6 ወራት አፈፃፀም | | | የ2013 በጀት ዓመት የ6 ወራት አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | ክንውን | % | ዕቅድ | ክንውን | % |
| | **የመንገዶች ግንባታ ፤ ማጠናከርና ማሻሻል** | 682 | 461 | 68 | 619 | 485 | 78 |
| | **የመንገዶች ጥገና** | 5814 | 4436 | 76 | 5600 | 4335 | 77 |
| | **ድምር** | **6496** | **4897** | **75** | **6219** | **4820** | **78** |

### 3.2.6 በበጀት ዓመቱ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ ተግዳሮት ያሳደሩ

ኢመባ የሚያስፈጽማቸው ፕሮጀክቶች በተለያዩ ምክንያቶች ሥራቸው ለጊዜው ሊቆም ወይም ሙሉ በሙሉ ሊቋረጥ ይችላል። ለፕሮጀክቶች ሥራ መቆም ወይም ሙሉ በሙሉ መቋረጥ በተደጋጋሚ መነሻ ከሚሆኑ ምክንያቶች ውስጥ የጸጥታ ችግር፣ የተቋራጩ ደካማ አፈጻጸም፣ የወሰን ማስከበር ችግር፣ ው.ዘ.ተ. ይጠቀሳሉ። በዚህም መሠረት በ2013 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት በአገራችን በነበረው ሁኔታ መነሻ ከዚህ ቀደም ከተለመደው ውጭ ከፍ ያለ ቁጥር ያላቸው ፕሮጀክቶች ሥራቸው ለጊዜው ሊቆም ወይም ሙሉ በሙሉ ሊቋረጥ ችሏል፤ አጠቃላይ ዝርዝራቸው ቀጥሎ ተመልክቷል።

#### 3.2.7.1 የተቋረጡ እና በመቋረጥ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች

| ተ.ቁ | የፕሮጀክት ስም | ሥራ ተቋራጭ | የተቋረጠበት ጊዜ | የተቋረጠበት ምክንያት | አሁን ያለበት ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዲቡ ወንዝ - ባዳይ ጨለለቃ | ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን | | የተቋራጩ ደካማ አፈጻጸም | ውሉ ተቋርጧል |
| 2 | አቦምሳ - አስኮ - ዲቡ ወንዝ | | | | |
| 3 | ጥቁር ዉኃ - ሐዋሳ | | ሰኔ 25/ 2020 | " | " |
| 4 | ደባርቅ-ቧሂት | አኪር | ሚያዝያ 2011 | የተቋራጩ ደካማ አፈጻጸም | በኢመባ ጎንደር ድስትሪክት ራስ ሀይል ፕሮጀክቱን ለማስጨረስ በዝግጅት ላይ |
| 5 | አይከል - ኪ.ሜ 69+000 | ሱር | | የጸጥታ ችግር እና የተቋራጩ ደካማ አፈጻጸም | ለሌላ ኮንትራክተር ለመስጠት በዝግጅት ላይ ነው |
| 6 | ሮቤ - ሴሩ /ሎት 2/ | ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን | ሰኔ 23/ 2020 | የተቋራጩ ደካማ አፈጻጸም | ለሌላ ኮንትራክተር ለመስጠት በዝግጅት ላይ ነው |
| 7 | ድሬ ማሻ ኮንት/1 | ኦርኪድ | ሰኔ 17/ 2020 | የተቋራጩ ደካማ አፈጻጸም | ውሉን የማቋረጥ ሂደት ላይ |
| 8 | ዱርጊ - ጊቤ ወንዝ (ኮንት 1) | ክፍሎም ገ/ህይወት | | የተቋራጩ ደካማ አፈጻጸም | ውሉ ተቋርጧል |
| 9 | ፈለገሰላ - አመያ - ጪዳ | | ሐምሌ 14/2020 | የመሬት መንሸራተት እና ያልተጠበቀ የትራፊክ ፍሰት በማጋጠሙ የዲዛይን ክለሳ ማስፈለግ | ለውሳኔ ቀርቧል |
| 10 | ነቀምት - ሶጌ -ከማሺ - ኮንቾ ኮን 3: KM 160 - ኮንቾ | አኪር | ሰኔ 17/2020 | የተቋራጩ ደካማ አፈጻጸም | ውሉን የማቋረጥ ሂደት ማጠናቀቅ |

### በህግ ማስከበሩ (በጦርነቱ) ምክኒያት ሥራቸው የቆመ ፕሮጀክቶች (21 ፕሮጀክቶች)

| ተ. ቁ | የፕሮጀክት ስም | ተ. ቁ | የፕሮጀክት ስም |
|---|---|---|---|
| 1 | ማይጨው - መሆኒ | 12 | አዲሸሁ - ዲላ - ሳምረ |
| 2 | ውቅሮ - አጽቢ - ኮንባ | 13 | ኮረም - ሰቆጣ - አቢአዲ ኮን 3(አበርገሌ - አገብ) |
| 3 | ውቅሮ - ነብለት | 14 | ኮረም - ሰቆጣ - አቢአዲ ኮን 1 |
| 4 | ነብለት - ፍላፍል | 15 | ፓዊ መገንጠያ - ኪ.ሜ 69 ሎት 1 |
| 5 | ራማ - ጪላ | 16 | መተማ - አብራጅራ |
| 6 | ሰመማ - እንደአባጉና | 17 | ኮረም - ሰቆጣ - አቢአዲ ኮን 2(ላሊበላ መገነጠያ - አበርገሌ) |
| 7 | አቢአዲ - ሰመማ | 18 | አዲአርቃይ - ጠለምት |
| 8 | ፍየል ዉሃ - ተከዜ ወንዝ ድልድይ | 19 | መቀሌ - ደጎላት - ኪ.ሜ 70 |
| 9 | አዲአቡን - ራማ | 20 | መቀሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ |
| 10 | ኩዊሀ - ማይመክደን | 21 | አዲረመት - አዲሂርዳ - በእከል |
| 11 | አዲረመት - ቁሊታ - አዲጎሹ | | |

በህግ ማስከበር (በጦርነት) ምክንያት በጊዚያዊነት ስራቸው የተቋረጠ 21 ፕሮጀክቶች ሲሆኑ ጠቅላላ ርዝመታቸው 1430.9 ኪ. ሜ ነው። በመሆኑም በ6 ወራት እንዲያከናዉኑ የተያዘላቸ ዕቅድ 124 ኪ.ሜ ሲሆን አፈፃፀማቸው 44 ኪ.ሜ ነው። ይህም የሆነው ባለፉት ሁለት ወራት በሰሜን የሃገራችን ክፍል በተፈጠረ የፀጥታ ችግር ምክንያት ምንም አይነት አፈፃፀም ማስመዝገብ ባለመቻሉ ነው ።

### 3.2.7.3 ተፈርመዉ ወደ ስራ ያልገቡ ፕሮጀክቶች (8 ፕሮጀክቶች)

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቶች ስም | በወቅቱ ወደ ስራ ያልገባበት ምክንያት |
|---|---|---|
| 1 | ሀዌላ-ቱላ-ወተራሬሳ-ወራንቻ | የአማካሪ መሀንዲስ ቅጥር ባለመጠናቀቁ |
| 2 | ዳየ - ጊርጃ - መልካ ደስታ እና መለያ መጀ | " |
| 3 | ሁምቦ ጠበላ-አባያ | " |
| 4 | ሻሸመኔ-ሃላባ | " |
| 5 | ደርሚ-ኪንቲቻ-ሻኪሶ | " |

በ2013 በጀት ዓመት ስድስት ወራት 345 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው ፕሮጀክቶች በበጀት ዓመቱ 2.6 ኪ. ሜ እቅድ ተይዞላቸው የአማካሪ መሀንዲስ ቅጥር ባለመጠናቀቁ ወደ ስራ አልገቡም።

## 3.3 የመንገድ ሀብት ማኔጅመንት አፈፃፀም

### 3.3.1 የድንገተኛ ሥራዎች አፈጻጸም

ባለፉት 6 ወራት ኢ.መ.ባ በሚያስተዳድራቸው መንገዶች ውስጥ በአስሩ ቅ/ዳይሬክቶሬቶች በ112 የተለያዩ ቦታዎች ላይ ክረምቱን ተከትሎ የድንገተኛ ጥገና ስራዎች ተከናውነዋል። እነዚህም ድንገተኛ ስራዎች በአጠቃላይ፣

- ✓ የመሬት ናዳ፣ የድልድዮች እና የፉካዎች መሰበር/በደለል መሞላት፣ የድልድይ ትከሻ መበላት (Bridge Abutment Scour) ፣የመንገድ መቋረጥ ፣ ስትራክተሮች በጎርፍ ምክንያት መሸርሸር፣ጎርፍ እና የመሳሰሉት አጋጥመዋል።

በእነዚህ መንገዶች ያሉ የደረሰውን ጉዳት በተወሰነ መልኩ ለመረዳት እንዲቻል ያጋጠሙ አደጋዎችን የሚያሳዩ የተለያዩ ምስሎች ቀጥለው ቀርበዋል።

የቀረቡት ምስሎች የሚያሳዩዋቸው አካባቢዎች/መንገዶች፣

- የድባጤ መገንጠያ - ድባጤ መንገድ
- አጣዬ ጨፋሮቢት
- ሰመራ አካባቢ











የእነዚህ ድንገተኛ አደጋዎች መከሰት በተወሰኑ አካባቢዎች የትራንስፖርት እንቅስቃሴው እንዲስተጓጎል፣ ሲከፋም ለተወሰኑ ቀናት እንዲቋረጥ አድርጓል። ሆኖም ችግሮች ለመፍታት በአስሩም ቅ/ዳይሬክቶሬቶቻችን በራስ ሃይል አቅም ና በአቅራቢያ ባሉ የግንባታ ሥራ ተቋራጮች ጋር በመቀናጀት የማስተካከያ እርምጃዎች በፍጥነት እንዲወሰዱ ተደርጓል።

ከተወሰዱት እርምጃዎች ውስጥ ለማሳያ ያህል፣

- ✓ የመሬት ናዳ ለተፈጠረባቸው በታዎች ናዳውን በመጥረግ መንገዶችን ክፍት ማድረግ (Clearing the debrise)
- ✓ የድልድዮች እና የፉካዎች መሰበር/በደለል መሞላት ለተፈጠረባቸው በታዎች ተለዋጭ መንገድ ግንባታ (Constuction of detour) ፣ ፉካዎችን መጥረግ (Silt Clearing) እና ጊዜያዊ የብረት ድልድይ ግንባታ (replace by bailey bridge) ስራ
- ✓ የድልድይ ትክሻ መበላት (Bridge Abutment Scour) በታዎች ላይ የተመረጠ ማቴሪያል በመጠቀም ጥገና ማድረግ
- ✓ የመንገድ መቋረጥ ያጋጠመ በታዎችን አፋጣኝ ጥገና በማድረግ ለትራፊክ ክፍት ማድረግ ስራ
- ✓ ስትራክተሮች በጎርፍ ምክንያት መሸርሠር ያጋጠመ በታዎች ላይ ጋቢዮን እና ግፊት ከል (Retaining Wall) መገንባት
- ✓ ጎርፍ ጉዳት ያደረሰባቸው በታዎችን ጎርፍ የመከላከያ ስትራክተሮች ግንባታ እና River Training Works ስራዎች ተከናውነዋል።

ድልድዮች በተጎዱባቸው አካባቢዎች ተለዋጭ የብረት ድልድዮች እንዲተኩ ተደርጓል።

| | |
|---|---|
|  |  |
| Shekosh Bailey Bridge | |

ይህም በመሆኑ ለአስቸኳይ ሥራዎች በገንዘብ ከብር 51,776,577.28 በላይ ወጪ ተደርጓል። በአሁኑ ወቅት መንገዶቹ ሁሉ ለትራፊክ ክፍት የሆኑ ሲሆን፣ በአንዳንድ በታዎች ላይ መጠነኛ ቀሪ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

ያጋጠሙ ችግሮች

- ✓ ለአስቸኳይ ጥገና ሥራዎች ማቴሪያል ለማግኘት የመስተዳድር አካላት ትብብር በሚጠበቀው ልክ አለመሆን
- ✓ ማህበረሰቡ ስለ መንገድ ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆን ( በከተማዎች አካባቢ ፉካዎች እና የውሃ መፋሰሻዎችን በተለያዩ ቆሻሻዎች እንዲደፈን ማድረግ ፣ በገጠር አካባቢ ለመስኖ በሚል ምክንያት መንገድ መቁረጥ)
- ✓ ለድንገተኛ ሥራዎች አመቺ የሆኑ ዘመናዊ መሳሪያዎች እጥረት እና ያሉት መሳሪያዎች ብልሽት።

### 3.3.2 የመንገድ ጥገና ሥራዎች አፈጻጸም

#### 3.3.2.1 የከባድ ጥገና ሥራዎች አፈፃፀም

የመንገዶች ከባድ ጥገና ሥራ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ለካፒታል በጀት ከሚመደብ በጀት የሚሠራ ሲሆን ሌሎች ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዋናነት በጣም የተጎዳን የላይኛው የመንገድ ንጣፍ /pavement/ መልሶ የመገንባት (የማንጠፍ) ሥራ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በ6 ወራት ውስጥ 307 ኪ.ሜ ታቅዶ 157 ኪ.ሜ (የዕቅዱ 51 በመቶ) ሊፈጸም ችሏል፡፡

#### 3.3.2.2 የመደበኛ እና ወቅታዊ ጥገና ሥራዎች አፈጻጸም

በመንገዶች ወቅታዊ ጥገና 560 ኪ.ሜ ታቅዶ 260 ኪ.ሜ (46 በመቶ) እና መደበኛ ጥገና 5,600 ኪ.ሜ ታቅዶ 4,335 ከ.ሜ (77 በመቶ) ተከናውኗል፡፡

ሠንጠረዥ 11:- የ6 ወራት የጥገና ሥራዎች አፈፃፀም

| ተ. ቁ | ንዑስ ተግባር | የበጀት ዓመቱ ግብ | የ6 ወራት | | | የዓመቱ ቀሪ ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | % | |
| **1** | **የመንገድ ጥገና ሥራዎች** | | | | | |
| 1.1 | የመንገደች ከባድ ጥገና | 844 | 307 | 157 | 51 | 687 |
| 1.2 | ወቅታዊ የመንገዶች ጥገና | 1,515 | 560 | 260 | 46 | 1255 |
| 1.3 | መደበኛ ጥገና | 13,303 | 4734 | 3919 | 83 | 9384 |
| | **ድምር** | **15662** | **5,600** | **4,335** | **77** | **11,326** |

በአጠቃላይ 6 ወራት አጠቃላይ አፈፃፀሙ 77% ሲሆን መደበኛ ጥገና 83% ከፍተኛ እንዲሁም ወቅታዊ 46%፣ ከባድ ጥገና 51% ዝቅተኛ አፈፃፀም ያሳዩ ሲሆን ለዚህም ዋነኛ ምክኒያቶች፡-

**ውስጣዊ ምክኒያቶች**

- የጥገና ማሽነሪዎች እጥረት (ዋቻ - ማጅ፣ ዲድግሳላ ያሎ፣ ቀብሪድሃር) ፣
- የሞብላዜሽን መዘግየት (ቆቦ - ላሊበላ ፕሮጀክት) ፣
- የማሽነሪ ማጓጓዣ(ሎቤድ) እጥረት፣
- በኮቪድ 19 ምክኒያት (በነቀምት ቅ/ዳ ለ2 ሳምንተ በኳራንቲን መዘጋት)

**ውጫዊ ምክኒያቶች**

- የኳሪ ሳይት እና የROW ችግር (ቱርሚ ሼክሽን)
- የፀጥታ ችግሮች (ጎንደር - ሁመራ፣ሚጋ- ዋጭሌ-ቡልቡል፣ሰለክላካ-ሽሬ፣አሰሳ - ሸርኮሌ - ኩሙሩክ)
- የኮንትራክተሮች ሞቢላይዜሽን መዘግየት(ዶዶላ-ሠ/ዋሻ-ሮቤ-ጎባ፣አፖስቶ-አገረሰላም፣ዶዶላ-ሠ/ዋሻ-ሮቤ-ጎባ) ፣
- የኮንትራክተሮች አቅም ማነስ (አዲጉደም-መቐለ-ውቅሮ፣የትኖራና ወጀል)

ሠንጠረዥ 12፡- የመደበኛ እና ወቅታዊ ጥገና ሥራዎች አፈጻጸም

| የዲስትሪክት ስም | የስራዉ ዓይነት | የፕሮጀክት ብዛት | የበጀት ዓመት ግብ | የ6 ወራት | | | የዓመቱ ቀሪ ስራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | አፈፃፀም | መቶኛ | |
| አለምገና | ወቅታዊ | 6 | 178 | 53 | 59 | 110 | 119 |
| | መደበኛ | 13 | 2110 | 692 | 765 | 111 | 1345 |
| | **ንዑስ ድምር** | **19** | **2288** | **745** | **823** | **111** | **1465** |
| አዲግራት | ወቅታዊ | 1 | 30 | 8 | 21 | 282 | 9 |
| | መደበኛ | 6 | 1723 | 673 | 690 | 103 | 1033 |
| | **ንዑስ ድምር** | **7** | **1753** | **681** | **711** | **105** | **1042** |
| ኮምቦልቻ | ወቅታዊ | 5 | 151 | 76 | 18 | 24 | 133 |
| | መደበኛ | 6 | 1142 | 443 | 248 | 56 | 894 |
| | **ንዑስ ድምር** | **11** | **1294** | **519** | **266** | **51** | **1027** |
| ደብረማርቆስ | መደበኛ | 4 | 941 | 428 | 256 | 60 | 685 |
| | **ንዑስ ድምር** | **4** | **941** | **428** | **256** | **60** | **685** |
| ጎንደር | ወቅታዊ | 5 | 207 | 49 | 21 | 44 | 185 |
| | መደበኛ | 3 | 1160 | 494 | 257 | 52 | 902 |
| | **ንዑስ ድምር** | **8** | **1366** | **542** | **278** | **51** | **1088** |
| ሻሸመኔ | ወቅታዊ | 8 | 436 | 217 | 115 | 53 | 321 |
| | መደበኛ | 9 | 1708 | 564 | 280 | 50 | 1428 |
| | **ንዑስ ድምር** | **17** | **2144** | **781** | **395** | **51** | **1749** |
| ነቀምት | ወቅታዊ | 2 | 68 | 26 | 15 | 55 | 53 |
| | መደበኛ | 7 | 816 | 248 | 207 | 83 | 609 |
| | **ንዑስ ድምር** | **9** | **884** | **275** | **222** | **81** | **662** |
| ድሬደዋ | ወቅታዊ | 2 | 290 | 114 | 3 | 2 | 287 |
| | መደበኛ | 8 | 1322 | 558 | 574 | 103 | 748 |
| | **ንዑስ ድምር** | **10** | **1612** | **672** | **577** | **86** | **1035** |
| ጅማ | ወቅታዊ | 4 | 86 | 17 | 8 | 46 | 78 |
| | መደበኛ | 8 | 763 | 201 | 154 | 77 | 609 |
| | **ንዑስ ድምር** | **12** | **849** | **218** | **162** | **74** | **687** |
| ሶዶ | ወቅታዊ | 3 | 69 | | | | 69 |
| | መደበኛ | 9 | 1618 | 433 | 488 | 113 | 1131 |
| | **ንዑስ ድምር** | **12** | **1687** | **433** | **488** | **113** | **1200** |
| ንዑስ ድምር | **ወቅታዊ** | **36** | **1515** | **560** | **260** | **46** | **1255** |
| | **መደበኛ** | **73** | **13303** | **4734** | **3919** | **83** | **9384** |
| **ድምር** | | **109** | **14,818** | **5,293** | **4,179** | **79** | **10,639** |

### 3.3.3 የመንገድ ጥገና ስራዎች በተቋራጮ

ሠንጠረዥ 13፡- የመደበኛ እና ወቅታዊ ጥገና ሥራዎች በተቋራጭ

| ተቋራጭ | የፕሮጀክቱ ቁጥር | የተቋራጭ ብዛት | ርዝመት | የ6 ወራት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | % |
| የግል ተቋራጮ | 6 | 5 | 641 | 322 | 313 | 97 |
| የሁሉም ድስትሪክት (ራስ ሃይል) | 82 | 10 | 11,829 | 4490 | 3852 | 86 |
| በግዥ ሂደት | 21 | - | 2348 | 482 | 14 | 3 |
| **ድምር** | **109** | **15** | **14818** | **5293** | **4179** | **79** |

**ማስታወሻ፡ በግዥሂደት ላይ ያለው አፈፃፀም ቀደም ብሎ የተከናወነ ሲሆን በአሁኑ ስዓት ግዥ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡**

### 3.3.4 የተሽከርካሪዎች ክብደት እና መጠን ቁጥጥር ሥራ እና የትራፊክ ቆጠራ አፈፃፀም

በ2013 በጀት ዓመት 6 ወራት ሁለት ጊዜ የመንገድ ትራፊክ ቆጠራ ለማድረግ ታቅዶ አንድ ጊዜ የተጠናቀቀ ሲሆን ሁለተኛው የትራፊክ ቆጠራ ዳታዉ እየተሰበሰበ ይገኛል፡፡

ከተሽከርካሪዎች ክብደት እና መጠን ቁጥጥር ጋር በተያያዘ የኮረና ቫይረስ በአገር ውስጥ ገቢና ወጪ ንግድ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽዕኖ መቀነስ በሚያስችል መልኩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየተከናወነ ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎን አዲስ የተቋቋሙት የሚዛን ጣቢያዎች የማጠናከር እና በሙሉ ስኬል ሥራ ለማስጀመር ጥረት እየተደረገ ነው፡፡


ሠንጠረዥ 14፡- ከክብደት በላይ ጭነት ቁጥጥር የስራ አፈፃፀም

| ዲስትሪክት | ሚዛን ጣቢያ | የተመዘነ የተሽከርካሪ ብዛት | ትርፍ ጭነት የጫኑ የተሽከርካሪ | ትርፍ ጭነታቸውን ያራገፉ ተሽከርካሪዎች ብዛት | ልዩ ፈቃድ የያዙ ተሽከርካሪዎች ብዛት | የተራገፈው ትርፍ ጭነት-በቶን | የግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጣቸው አሽከርካሪዎች) | ፍርድ ቤት ቀርበው የተወሰነ ባቸው | የቅጣት መጠን በብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አለምገና | ሞጆ | 9,216 | 2,040 | 876 | - | 5,708 | 595 | 898 | 496,068 |
| | ሆለታ | 11,927 | 716 | - | - | 724 | 577 | 726 | 116,032 |
| | ሱልልታ | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | ሰንዳፋ | 7,757 | 89 | 323 | - | 33 | 206 | 30 | 12,823 |
| | ዲማ | 244 | 143 | - | - | - | - | - | - |
| ድሬዳዋ | ደንገጎ | 2,646 | 371 | 140 | - | 159 | 483 | 229 | 486,792 |
| | አዋሽ | 16,481 | 2,081 | 219 | - | 109 | 1,054 | 2,057 | 2,038,214 |
| ጅማ | ጅማ | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ኮምቦልቻ | ኮምቦልቻ | 1,431 | 1 | - | - | - | 70 | 1 | 550 |
| | ሰመራ | 12,480 | 9,777 | 95 | | 1,065 | 8,201 | 534 | 1,647,081 |
| ሻሸመኔ | ሻሸመኔ | 3,915 | 113 | - | - | - | 1,120 | 83 | 25,540 |
| ደ/ማርቆስ | ጢቅ | 805 | 766 | 17 | | 56 | 892 | 43 | 40,420 |
| አዲግራት | ኩዊሃ | 792.00 | - | - | - | - | - | - | - |
| ጎንደር | ወረታ | 1,440 | 115 | 9 | 37 | 12 | 225 | 48 | 36,440 |
| **ድምር** | | **69,134** | **16,212** | **1,679** | **37** | **7,866** | **13,423** | **4,649** | **4,899,960** |

**በ8ቱ ዲስትሪክቶች በተደረገ 69,134 የተሽከርካሪዎች ከክብደት በላይ የጭነት ቁጥጥር**

- ✓ 75 በመቶ ግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጣቸው አሽከርካሪዎች
- ✓ 9.3 በመቶ ትርፍ ጭነታቸውን ያራገፉ ተሽከርካሪዎች
- ✓ 0.2 በመቶ ልዩ ፈቃድ የያዙ ተሽከርካሪዎች
- ✓ 49 በመቶ ትርፍ ጭነታቸውን ያራገፉ (በቶን)
- ✓ 26 በመቶ ፍርድ ቤት የቀረቡ
- ✓ አጠቃላይ የቅጣት መጠን 4.9 ሚሊዮን ብር

**ከክብደት በላይ ጭነት ቁጥጥር አፈፃፀም የ1ኛ እና የ2ኛ ሩብ ዓመት ንፅፅር**




## 3.3.5 የመንገድ ደህንነት ሥራዎች አፈጻጸም

2013 በጀት ዓመት የመንገድ ደህንነት ስራዎች ጥራቱ የተጠበቀ እና ቀጣይነት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ ፕሮጀክቶች ሲቀረፁ የታለመላቸውን ግብ እንዲያሟሉ በማድረግ የመንገድ ተጠቃሚ ወጪ እና ጊዜ መቆጠብ፣ የተሽከርካሪ አደጋን መቀነስ እንዲሁም ለመንገድ ግንባታ ስራ የወጣው ወጪ ውጤታማነት (better value for money) በማስገኘት የመንገድ ኔትወርክ ጠቀሜታን ለማረጋገጥ የሚከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ በ6 ወራት የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

- ✓ ደ/ማርቆስ፣ ድሬዳዋ፣ ሻሸመኔ፣ ሰዶ እና ነቀምት መንገድ ኔትዎርክ ስር በሚገኙ የመንገድ ፕሮጀክቶች የመንገድ ደህንነት ስራዎች (ኪ. ሜ ፖስት፣ ጋይድ ፖስት፣ የቀለም ስራ፣ ጋርድ ሬይል፤ ዜብራ ማቋረጫ)

- ✓ የተከናዉ ሲሆን ለእነዚህ ተግባረት 162,856,169.64 ሚ. ብር ወጭ ለማድረግ ታዕዶ 65970328.27 ሚ. ብር (40.5%) ወጭ ተደርጓል፡፡

***የመንገድ ደህንነት ሥራዎች***



# ምዕራፍ አራት

# የዘርፈ ብዙ ሥራዎች አፈፃፀም

4

## 4.1 የሴቶች እና ወጣቶች ጉዳይ አፈጻጸም

ከሴቶችና ወጣቶች ጋር በተያያዘ የሚሰራውሩ ሥራዎች በዋናነት ሁለት ገጽታ አለው፤ አንድም አቅማቸውን ማጎልበት ሲሆን ሁለተኛው በየደረጃው ተጠቃሚነታቸው ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በ6 ወራት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ስርዓተ ፆታን አካቶ መስራት እና የዜጎችን እኩል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከታያዙት ዕቅድ ውስጥ የዋና ዋና ሥራዎች አፈጻጸም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 15: የሴቶች እና ወጣቶች ጉዳይ አፈፃፀም

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት ዝርዝር | ዕቅድ | ክንውን | መቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በሥራ ክፍሎች የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች እንዲሁም የኮንትራት ውሎች የስርዓተ-ፆታ አካታችነታቸውን መገምገምና ግብረመልስ መስጠት፣ | 8 | 6 | 75 | |
| 2 | በመንገድ ፕሮጀክቶች ውስጥ ወጣቶች እና ሴት ሰራተኞች ከጎጂ ድርጊቶችና ጾታዊ- ትንኮሳን ለመታደግ በህግጋቱና መከላከል ዙሪያ ግንዛቤ/ስልጠና ማሰጠት/መስጠት፣ | 2 | 1 | 50 | በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት እንደሚገባው አልተሰራም |
| 3 | በመስክ ምልከታ ጊዜ የፆታ ጥቃት አጋላጭ ሁኔታዎችን መለየትና እንዲፈቱ ከኮንትራክተር፣ከኮንሰልታንት እና በአካባቢው የመንግስት ተቋማት ጋር በጋራ መስራት፣ ስለጀንደር ሴንሲታይዜሽን፣ እኩል የስራ ክፍያ፣ የሴቶች በተፈጥሮ ልዩ ባህሪያቸው ምክንያት ምቹ ሁኔታ/የስራ ማቅለያ መሳሪያዎች/ እንዲቀርቡላቸው በመስክ ምልከታ የውውይትና ክትትል ግብረ መልስ መስጠት፣ | 16 | 6 | 38 | በነቀምት-ቡሬ ኮንት-2 እና በምስራቅ ሪጅን የሚገኙ 5 ፕሮጀክቶች ላይ የመስክ ምልከታና እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት የስልጠና እና የውይይት መድረክ ማከናወን ተችሏል፡፡ |
| 4 | በስርዓተ-ጾታ እኩልነት፣በሴቶች እና ወጣቶች ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ዙርያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፅሁፎች /ብሮሸሮች/ ማዘጋጀትና በተቋሙ ወቅታዊ መጽሄት /በስልጣኔ-በር/ እና ዌብሳይት ላይ እንዲታተምና እንዲተላለፍ ማስፈጸም፣ | 1 | 4 | ++ | በህጻናት እና በስርዓተ-ጾታ ጥቃት ምንነትና ዓይነቶች በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ያተኮሩ ርእሶች በዲጂታል ሳይነጅ ማስተላለፍ ተችሏል |
| 5 | ወጣቶችና ሴት ሠራተኞች ራሳቸውን በትምህርት እንዲያጎለብቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት | 80 | 76 | 95 | በነፃ/ቅናሽ የትምህርት ክፍያ ተጠቃሚ የሆኑ ሰራተኞች፡-<br>✓ 45 ሰራተኞች የማስተር ፕሮግራም እንዲከታተሉ ለ2 የግል ተቋማት ተልኳል፡፡<br>✓ 31 የመ/ቤቱ ሰራተኞች PCOC ስልጠና ወስደው የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ስምምነት ላይ መድረስ ተችሏል፡፡ |


| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት ዝርዝር | ዕቅድ | ክንውን | መቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 6 | የመ/ቤቱ የህፃናት ማቆያ ማዕከል አገልግሎቱን ለማስጀመር እና ግብዓት እንዲላ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፣ | 1 | 0.95 | 95 | በኮረና ወረርሽኝ ምክንያት የህፃናት ማቆያ ማዕከሉን ሥራ ማስጀመር እንዲዘገይ ስለተደረገ ግንባታው ይህንኑ ታሳቢ ባደረገ መልኩ የማሻሻያ ሥራ እየተከናወነለት ነው፡፡ አገልግሎት ለማስጀመር የሚያስፈልጉት የሰዉ ሃይልና ግብዓት/ቁሳቁስ/ የማሟላት/ግዢ የመፈፀም ስራ ተከናውኗል፡፡ |
| 7 | ለሰራኞች ለህፃናት እና ለአካል ጉዳተኞች የማሕበራዊ እና የበጎ አድራት ድጋፍ ማድረግ | በ6 ወራት ውስጥ ለ55 ሰራተኞች፣ ህፃናትና የስራ ሃላፊዎች 755,710 ብር ድጋፍ ተድርጓል፡፡ | | | |




በፆታዊ ጥቃት ዙሪያ ስልጠና ሲሰጥ



የኢ.መ. ባ ቤተሰብ ደም ልገሳ ሲያካሂዱ



ሠንጠረዥ 16፡ በኢመባ በመንገድ ግንባታ እና መንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች በ2013 በጀት አመት በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል

| ፕሮጀክቶች ብዛት | የተፈጠረ የሥራ ዕድል በችሎታ ደረጃ | የተፈጠረ የሥራ ዕድል በጾታ ስብጥር | | | የተፈጠረ የስራ ዕድል በቋሚ እና በኮንትራት | | | | | | የተፈጠረ የሥራ ዕድል በጾታና በዕድሜ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ቋሚ | | | ኮንትራት | | | ዕድሜ ≤29 | | | ዕድሜ ≥30 | | |
| | | ሴት | ወንድ | ድምር | ሴት | ወንድ | ድምር | ሴት | ወንድ | ድምር | ሴት | ወንድ | ድምር | ሴት | ወንድ | ድምር |
| **239** | ፕሮፌሽናል | 1,698 | 12,153 | 13,851 | 969 | 7,547 | 8,516 | 729 | 4,606 | 5,335 | 1,044 | 6,214 | 7,258 | 654 | 5,939 | 6,593 |
| | በከፍል-ፕሮፌሽናል | 2,401 | 9,555 | 11,942 | 686 | 3,236 | 3,922 | 1,715 | 6,319 | 8,020 | 1,556 | 5,690 | 7,240 | 845 | 3,865 | 4,702 |
| | ፕሮፌሽናል ያልሆኑ | 6,501 | 20,308 | 26,990 | 1,086 | 4,528 | 5,664 | 5,415 | 15,780 | 21,326 | 4,386 | 11,169 | 15,729 | 2,115 | 9,139 | 11,261 |
| | **ጠቅላላ** | **10,600** | **42,016** | **52,783** | **2,741** | **15,311** | **18,102** | **7,859** | **26,705** | **34,681** | **6,986** | **23,073** | **30,227** | **3,614** | **18,943** | **22,556** |

**ማስታወሻ፡ በአገራችን ሰሜኑ ክፍል በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክኒያት በአዲግራት ዲስትሪክት ያለው የስራ እድል ፈጠራ አልተካተተም፡፡**

በ2013 በጀት ዓመት ስድስት ወራት በ 17 የኮንስትራክሽን፣ የጥገና እና የማስልጠኛ ማዕከላቶች ላይ ባሉ **239** ፕሮጀክቶች ለ**52,783** ሰራተኞች የስራ እድል የተፈጠረ ሲሆን **10,600** ሴት **(20 በመቶ)** እና **42,041** ወንድ **(80 በመቶ)** ናቸው።

